16

የመንፈሳዊው መሪ ኃላፊነቶች

የቀሪውንም ነገር ሳልቆጥር፣ ዕለት ዕለት የሚከብደብኝ የአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ አሳብ ነው።
2ኛ ቆሮንቶስ 11:28

መሪነት ለሚለው ቃል ኢየሱስ የሰጠው ትርጉም አገልጋይነት የሚል ነበር፤ እንደ እውነቱ ከሆነ በዓለማዊውም ሆነ በመንፈሳዊ አሠራር አንድ መሪ ይህንኑ ነው መሆን ያለበት። ሎርድ ሞንትጎመሪ የተባሉ የጦር መሪ የጦር ሜዳ ውሎአቸው «አንድ መሪ ከበላይ ባለሥልጣን መመሪያ እየተቀበለ በቅን ልቦና ሠራዊቱን ማገልገል አለበት። ልታይ ልታይ ማለትንና ደምቆ መታየትንም መፈለግ የለበትም» ወደሚል አቋም እንዳደረሳቸው ይናገራሉ።

ዶክተር ኤ.ቢ. ብሩስ የተባሉ ሰው ደግሞ አሥራ ሁለቱን ሐዋርያት ለማሠልጠን ኢየሱስ ስለ ተጠቀመበት ዘዴ ባዘጋጁት መጽሐፍ «ዓለማውያን መሪዎች ሰዎችን ይገዛሉ፤ ባለሥልጣኖችን ሌሎች ያገለግሉዋቸዋል። በመለኮታዊው አሠራር ግን መሪዎች የሕዝብ አገልጋዮች ናቸው» ብለዋል። የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን መንግሥት ተልዕኮ ለመፈጸም አገልጋይ ሆነ። አብያተ ክርስቲያናት፣ ሚስዮናዊ ድርጅቶችና ክርስቲያን ግለሰቦች የተሰጣቸውን አገልግሎት ለመፈጸም ይህን ምሳሌ ማድረግ ይኖርባቸዋል። እውነተኛ መሪ በዋነኝነት ደረጃ ከራሱ ምኞትና ደስታ ይልቅ ለሌሎች ደኅንነት ቅድሚያ ይሰጣል። በድካማቸው፣ በችግራቸውና በሚያሳስባቸው ነገር ሁሉ ያዝናል፤ ይራራል። አዘኔታውና ርኅራኄው ግን የሚያበረታታና ካሉበት ሁኔታ የሚያወጣ እንጂ መለሳለስ ላይ የተመሠረተ መሆን የለበትም። ምን ጊዜም ቢሆን እምነትና ትምክህታቸውን እግዚአብሔር ላይ እንዲያደርጉ ይመክራል፤ ያበረታታል። ማንኛውንም ችግር ሌሎችን ለማገልገል እንደ መልካም አጋጣሚ ይጠቀምበታል። ታላቁ ሙሴን እንዲተካ እግዚአብሔር የመረጠው ኢያሱ ቀድሞውኑ ታማኝ አገልጋይነቱን ያስመሰከረ ሰው እንደነበረ መረዳት ተገቢ ነው (ዘጸ. 33:11)።

ሐድሰን ቴለር የተዋጣለት መንፈሳዊ መሪ ነበር። ይህን የመሪነት ችሎታውን አስመልክቶ እርሱን እንዲተካ የተመረጠው ሰው ሲናገር እንዲህ ብሎ ነበር፦

አብረነው ለምንሠራ ሰዎች ሁሉ የሚያስብና የሚራራ ነበር፤ ምን ጊዜም ቢሆን ምቾትና ደህንነታችን እንዲሟላ ይፈልጋል። እርግጥ ነው፤ ታላቅ መሥዋዕትነትን ከፍሎአል፤ ለሥራው ሌት ከቀን ይደክም ነበር፤ ይሁን እንጂ ይህ እርሱ የደረሰበት ደረጃ ላይ ያልደረስነው እኛ ላይ ጨካኝ አላደረገውም። ይልቁንም ያዝንልን ይራራልን ነበር። ውድቀትና ድካማችንን በትዕግሥት በመቀበል ከዚያ ወጥተን ወደ ላቀ ደረጃ እንድንደርስ በሚቻለው ሁሉ ያግዘን ነበር።

ሌላው የመንፈሳዊ መሪ ኀላፊነት ደግሞ ሥርዓት ማስያዝ ሲሆን በመሠረቱ ይህ ቀላል ሥራ አይደለም። እንዲህ ያለውን ጉዳይ ሰዎች በደስታ አይቀበሉም። እምነትን፣ ሥነ ምግባርንና ክርስቲያናዊ አሠራርን አስመልክቶ ማንኛውም ቤተ ክርስቲያን ወይም መንፈሳዊ ድርጅት የራሱ መመሪያ ይኖረዋል። ሰዎች በፍቅርና በመንፈሳዊ ሕይወት እንዲታነጹ ከተፈለገ ሥርዓት ማስያዝ በጣም አስፈላጊ ነው።

ሌሎችን ሥርዓት በማስያዝ ረገድ ልንከተለው ስለሚገባ አሠራር ጳውሎስ ሲጽፍ «ወንድሞች ሆይ፣ ሰው በማናቸውም በደል ስንኳ ቢገኝ መንፈሳውያን የሆናችሁ እናንተ እንዲህ ያለውን ሰው በየውሃት መንፈስ አቅኑት፤ አንተ ደግሞ እንዳትፈተን ራስህን ጠብቅ።» ብሎአል (ገላ. 6፡1)። ሥርዓት የማስያዝ፣ ወይም ሥርዓትን የማስጠበቅ ዋናው መሠረት ፍቅር ሊሆን ይገባል። «እንደ ወንድም ገሠጹት እንጂ እንደ ጠላት አትቁጠሩት» (2ኛ ቆሮ. 2፡8)። ካለበት ድካም እንዲወጣ አንድን ሰው በፍቅር ካገዝነው እርሱም በተራው ሌሎችን በፍቅር ያግዛል፤ ለሌሎች ድካም ይራራል። ከነቃፊነትና ሰዎችን በድካማቸው ለመያዝ ከምናደርገው ክትትል ይልቅ የየዋህነት መንፈስ ከፍተኛ ውጤት ያስገኛል።

በደል ላይ ያለ ወንድምን ሥርዓት ለማስያዝ እርምጃ ከመውሰዳችን በፊት አምስት ነጥቦችን ማገናዘብ ይኖርብናል፡- 1ኛ) እርምጃውን የምንወስደው ያለምንም ወገናዊነት ዝንባሌ ብዙ ካጠናንና ካሰብንበት በኋላ መሆን አለበት፣ 2ኛ) የምንወስደው እርምጃ ግለሰቡንና አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴውን የሚጠቅም ሆኖ ሲገኝ ብቻ መሆን አለበት፣ 3ኛ) እርምጃውን የምንወስደው በእውነተኛ ፍቅርና ለጽድቅ በመቆርቆር መንፈስ መሆን አለበት፣ 4ኛ) ምን ጊዜም እርምጃውን የምንወስደው በደል ያደረሰውን ሰው መንፈሳዊ ሕይወት ለመጥቀምና መርዳት በሚያስችል መልኩ መሆን አለበት፣ 5) እርምጃውን የምንወስደው ብዙ በመጸለይና በጌታ ፊት ብዙ በመቆየት መሆን አለበት።

ምሪት መስጠት ሦስተኛው ኀላፊነት ነው። በመጀመሪያ ደረጃ፣ መሪው የሚሄድበትን መንገድ ማወቅና እንደ ምሥራቃውያን እረኛ ሁሉ አብረውት ያሉትን ፊት ፊታቸው እየሄደ መምራት ይኖርበታል። የእረኞች አለቃ የሆነው ክርስቶስ ይደረገውም ይህንኑ ነበር። «የራሱ የሆኑትንም ሁሉ ካወጣ በኋላ ፊት ፊታቸው ይሄዳል» (ዮሐ. 10፡4 - አ.መ.ት)። «እውነተኛ መሪ» ይላሉ ኤ.ደብልዩ ቶዘር «የእግዚአብሔርን ድምፅ ይሰማል፤ በድምፁ መሠረት ይንቀሳቀሳል፤ ሌሎችንም ያንቀሳቅሳል።» ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ሲጽፍ - «እኔ የክርስቶስን ምሳሌ እንደምከተል እናንተም የእኔን ተከተሉ» ብሎአቸዋል (1ኛቆሮ. 11፡1 - አ.መ.ት)። መንፈሳዊ መሪ ማንን እየተከተለ እንደሆነና ወዴት እንደሚሄድ ያውቃል፤ ስለዚህም ሌሎች እንዲከተሉት በልበ ሙሉነት ይጣራል።

ሰዎችን መምራት ሁልጊዜ ቀላል አይደለም፤ መንፈሳዊነት ቢኖራቸውም እንኳ አንዳንዶች የያዝነው መንገድ ትክክል ነው የሚል ግትር አቋም ሊኖራቸው ይችላል። ስለሆነም መሪው የራሱን አስተያየትና አመለካከት በግዳጅ ሌሎች ላይ መጫን አይኖርበትም። ይህን በተመለከተ አንድ እውቅ ሰው ሲጽፍ እንዲህ ብሏል፦

> «ምንም እንኳ የምንከተለው መንገድ ትክክል እንደሆነ በናውቅም፤ ተግባር ላይ ቢውል የሚሰጠውን ጥቅም በሚገባ ብንገነዘብም፤ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ወገኖች የሚቃወሙት ሆኖ ከተገኘ ልናዘገየው ይገባል። ሐድሰን ቴለር የተባለ ሚስዮናዊ መሪ ያወጣቸውን እቅዶች ብዙ ጊዜ እንደገና ያሻሻላቸው ነበር፤ አንዳንድ ጠቃሚ ነገሮችን ከማድረግም የተቆጠበበት ወቅት ነበር፤ ያም ሆኖ ግን ሆን ብለው የሚቃወሙ ሰዎችን አላጣም፤ መደረግ የነበረበት ነገር በወቅቱ ቢደረግ ኖሮ ይወገዱ የነበሩ ችግሮችም እንዳሉ ነበር። ይህን እንጂ ጉዳዩን በትዕግሥት በመቀበልና ብዙ በመጸለይ የኋላ ኋላ እቅዶቹን ተግባራዊ ማድረግ ችሎአል»።

ዓላማ ላለው ጉዳይ ሌሎችን መቀስቀስና ማነሣሣት ከመንፈሳዊ መሪ የሚጠበቅ ጠቃሚ የሥራ ድርሻ ነው። አንዳንዶች አዳዲስ ነገሮችን ከማቀድና ከመተግበር ይልቅ ነገሮችን ባሉበት ሁኔታ የማቆየት ችሎታ ይኖራቸዋል፤ አዳዲስ ነገሮችን ከማፍለቅ ይልቅ ቀደም ያሉትን ነገሮች ሥርዓት በማስያዝ በኩል የተዋጣላቸው ሊሆኑ ይችላሉ። እውነተኛ መሪ ግን የአዳዲስ ውጥኖች ራእይ ሊኖረው ይገባል፤ ከሌሎች ጋር በመሆን ራእዩን ተግባር ላይ የማዋል ችሎታም ሊኖረው ይገባል። ሁኔታዎችን ባሉበት መልኩ የሚይዝ ወይም

የሚጠብቅ ብቻ ሳይሆን፣ አዳዲስ ውጥኖችንም የሚያፈልቅ ሊሆን ይገባል። ብዙዎቻችን ችግር እንዳያስከትልብን በመፍራት አንዳንድ እርምጃዎችን አንወስድም። ጳውሎስ ግን የዚህ ዓይነት ሰው አልነበረም፤ ችግር እንደሚያስከትልበት ቢያውቅም በጥንቃቄና በጸሎት መንፈስ ቆራጥ እርምጃዎችን ይወስድ ነበር።

መሪው ለሥራው መሻሻል የሚረዱ አዳዲስ እቅዶችን ማውጣት መቻል አለበት፤ ያ ካልሆነም ሌሎች የሚያወጡትን እቅድ መቀበል ይኖርበታል። ይሁን እንጂ ፊት ለፊት በመሄድ ጉዳዮችን ማስፈጸምና አብረውት ያሉትን መምራት ግን የእርሱ ኀላፊነት መሆን አለበት። እርሱ ራሱ አድራጊ እንጂ በሌሎች እስኪደረግ የሚጠብቅ ሊሆን አይገባም። ለሥራው መሻሻል ይጠቅማሉ ብሎ የሚያስባቸውን አዳዲስ ዘዴዎች ይቀበላል። የአዳዲስ አሳቦችን ጠቀሜታ በጥንቃቄ ይመረምራል።

አዳዲስ ነገሮችን ከመፍራትና ችግር እንዳይደርስብን ከምናደርገው አጉል ጥንቃቄ የተነሣ እርምጃ አንወስድም፤ ከዚህም የተነሣ ሥራው ይጎዳል። በዘመናት የነበሩ ታላላቅ የእግዚአብሔር ሰዎች ግን ችግር እንደሚኖር ቢያውቁም የእምነት እርምጃን ከመውሰድ ወደ ኀላ የሚሉ አልነበሩም። ለምሳሌ ያህል ሐድሰን ቴለር የወሰደውን የእምነት እርምጃ ብዙዎች ተችተው ነበር፤ ጨርሶ ተግባር ላይ ሊውል እንደማይችልም ተናግረው ነበር። ይህ ግን በፍጹም አላስበረገገውም፤ ዛሬ ማን ትክክል እንደ ነበር ታሪክ መስክሮአል። በቤተ ክርስቲያን ታሪክ የተከናወኑ ታላላቅ ሥራዎች እግዚአብሔር በነካቸውና የእምነት እርምጃ በወሰዱ ሰዎች የተከናወኑ ናቸው፤ አደጋ እንደሚገጥማቸው ቢያውቁም እርሱ የሰጣቸውን ራእይ እውን ከማድረግ አላወላወሉም።

ትልቁ ውድቀታችን እርምጃ መውሰድ ሲገባን ምንም አለማድረጋችን ነው፤ የአዳዲስ አሳቦችን ትክክለኛነት ወይም ስሕተት ፈትነን ለማወቅ መፍራታችን ነው። አንድ ጊዜ በሚሲዮናዊ ሥራ ተሰማርቶ ያለ ሰው ወደ ኀላ ዘወር ብሎ ሕይወቱን ሲመለከት ካደረጋቸው ጥፋቶች ብዙዎቹ ድፍረት ያለው እርምጃ ባለመወሰዱ የተፈጸመ መሆናቸውን ለዚህ ጸሐፊ ነግሮታል። በእግዚአብሔር መንግሥት ግንባር ቀደሙን ቦታ ይዘው የምናያቸው ሰዎች ፈሪዎችና እርምጃን ለመውሰድ የሚያመነቱ አልነበሩም።

አንድ መሪ አብረውት ያሉ ሰዎችን ምክርና ማስጠንቀቂያ ችላ ማለት የለበትም። ብዙ ጊዜ የማያስፈልግ ስሕተትን ከመፈጸም ሊያድኑት ይችላሉ። ይሁን እንጂ ያለው ራእይ ከእግዚአብሔር መሆኑን እርግጠኛ ከሆነ የሰዎች ምክርና ማስጠንቀቂያ እርምጃ

ከመውሰድ እንዳያስናክለው መጠንቀቅ አለበት። እርሱም ሆነ ሌሎች ማድረግ የሚገባቸውን በወቅቱ ሳያደርጉ እንዳይቀሩ ጥንቃቄ ማድረግ አለበት።

የተጣለበትን ኃላፊነት በፈቃደኝነት መወጣት የአንድ እውነተኛ መሪ ዓይነተኛ ምልክት ነው። ለዚህ ዝግጁ ካልሆነ ግን ኀላፊነቱን ለመቀበል አይበቃም ማለት ነው። ከባድ ጥረት የሚጠይቅ ሥራን የሚሸሽ ሰው፣ በዚያው መጠን ሌሎችን የመምራት ብቃቱም ውሱን ይሆናል።

የታላቁ መሪ ሙሴን ፈለግ ተከትሎ ሕዝቡን እንዲመራ ኀላፊነት ሊሰጠው ኢያሱ ለመቀበል አላመነታም። በዚህም የመሪነት ብቃቱን አሳይቶአል። ከሙሴ ይልቅ ኢያሱ ብቁ አለመሆኑን ለመናገር ብዙ ምክንያቶችን ማቅረብ ይችል ነበር፤ እርሱ ግን የሙሴን በደል በድጋሚ መፈጸም አልፈለገም። ከዚህ ይልቅ የተጣለበትን ኀላፊነት ሳያመነታ ተቀብሎ ራሱን ለሥራው ሰጠ።

ኤልያስ ወደ ሰማይ ከተወሰደ በኋላ የእርሱን ስፍራ ለመተካት ኤልሳዕ ያለ ምንም ማመንታት ኀላፊነቱን ተቀብሎአል። የነቢዩ መጎናጸፊያ ሲያርፍበት ከዚሁ ጋር አብሮ ኀላፊነቱም ወድቆበታል። እዚህ ላይ ትልቁ ትኩረት የሚሰጠው መለኮታዊው ጥሪ ነው፤ አንድ ሰው መለኮታዊ ጥሪ እንዳለው እርግጠኛ ከሆነ ከእግዚአብሔር የተመደበለትን ኃላፊነት ለመቀበል አይፈራም።

ታላላቅ የእግዚአብሔር ሰዎችን ሕይወት ማጥናትና ለመንፈሳዊ ውጤታማነታቸውም አስተዋፅኦ ያደረጉ ነገሮችን መረዳት የአንድን መሪ ልብ የማነቃቃት ባሕርይ አለው።

አንድ እውቅ መንፈሳዊ ሰው ምንም እንኳ ከፍተኛ የሥራ ጫና እንደነበረባቸው ቢታወቅም ተግባራቸውን በመወጣት ረገድ የረዱዋቸው መመሪያዎችን አስፍረዋል። መመሪያዎቹ ሐቁን እንድናይ ከማስቻላቸውም በላይ እርምጃ ለመውሰድም የሚያነሳሱ ናቸው። እርሳቸው የኖሩት ካለንበት በተለየ ዘመንና ሁኔታ ቢሆንም፣ መመሪያዎቹ ዛሬም ቢሆን ምን ያህል ጠቃሚ እንደሆኑ መመልከት ይቻላል።

- ዋነኛውን የዕለት ሥራ ከመጀመር አለመዘናጋት፤ ከዛሬ ነገ አለማለት።
- በሥራው ብዛት ወይም በጊዜ እጥረት ከማማረር ይልቅ ጊዜን በአግባቡ ተጠቅሞ ኃላፊነትን መወጣት።
- ምላሽ የሚያሻቸው ደብዳቤዎች በብዛት ቢመጡም አለመሰላቸት ወይም አለማጉረምረም።

- በጣም የደከመ መስሎ በመታየት ያለብንን የሥራ ብዛት ከመጠን በላይ አለማጋነን፤ ይልቁንም ደስ እያለን በነጻነት መሥራት።
- ስለ ሥራው ብዛት ይህን ያህል አለማሰብና ባለፈ ክንውን አለመኩራራት።
- የአንድን ሰው ሥራ መመርመር ከመጀመራችን በፊት ሰውየውን ለመውደድ የሚያስችል የእግዚአብሔር ፍቅር እንዳለን ማረጋገጥ። ምናልባት እንኪ ሥራው የጠበቅነውን ያህል ሆኖ ባይገኝ ጥቃቅን ስሕተቶችን ለማለፍ መቻልና መሥራት የሚችለውን ሥራ መስጠት። ያን ካላደረግን ግን ጥናትና ምርምራችን ሁሉ ፍሬ ቢስ ከመሆኑም በላይ ሰዎችን ሊያስቆጣ ይችላል።
- ስለ ሌሎች ምንም አለማውራት፤ ሳይመረምሩ ሁሉንም አለማመን፤ የሰሙትን ሁሉ አለመናገር።
- ባለፈው ጊዜ ስላደረግነው ከአለቆቻችን ወይም ከሌሎች ጓደኞቻችን ምስጋናና ክብርን አለመፈለግ።
- ሃሳባችንን እንድንሰጥ ባለመጠየቃችን ወይም ያቀረብነው አሳብ ተቀባይነት በማጣቱ አለመከፋት።
- ራስህን ከሌሎቹ ጋር እያወዳደርህ አብረውህ ካሉት በልጠህ ለመታየት አለመፎካከር።
- የሰዎች ንግግር አቅጣጫ ባንተና በሥራህ ላይ እንዲሆን አለመሞከር።
- ከማንም ቢሆን ውለታን እንድመልስልህ፤ ችሮታ እንዲያደርግልህ፤ እንዲያዝንልህ ወይም ጮሽ እንዲልህ አለመጠበቅ።
- የሚሰነዘረውን ወቀሳ ብቻህን መቀበል እንጂ ሌሎችን ተጠያቂ አለማድረግ።
- አንተ ባወጣኸው እቅድ ሌላው ቢመሰገንና ሥራውንም እንዲሠራ ቢሰጠው ከመበሳጨት ይልቅ ማመስገን።

17

መንፈሳዊ መሪነት ሲፈተን

እግዚአብሔር አብርሃምን ፈተነው።
ዘፍጥረት 22:1

ከዚያ ወዲያ ኢየሱስ ከዲያብሎስ ይፈተን ዘንድ መንፈስ ወደ ምድረ በዳ ወሰደው።

ማቴዎስ 4:1

መሪ ለመሆን መፈተን እንዳለ ሁሉ መሪ ከሆኑ በኋላም እንዲሁ መፈተን ይኖራል። «እግዚአብሔር አብርሃምን ፈተነው» የሚለው ታሪካዊ እውነት ብቻ ሳይሆን ለምን ጊዜም የሚሆን ዘላለማዊ መርሖ ነው። መንፈሳዊ ሥልጣንን የተቀበለ ሰው ውሎ አድሮ መፈተኑ የማይቀር ነው።

መደራደር ወይም ከአቋም ማፈግፈግ

መደራደር ሲባል ከሌሎች ጋር ለመስማማት ሲባል አንዳንድ የምናምንባቸውን ነገሮች በከፊልም ቢሆን ማለሳለስ ማለት ነው። ሌሎችን ለማስደሰት ስንል መመሪያችንን ወይም መለኪያ ሚዛናችንን ዝቅ ካደረግን እየተደራደርን ወይም እያፈገፈግን ነው ማለት ነው፤ እንደዚያ ከሆነ ደግሞ ወደ ፊት ሳይሆን ወደ ኋላ እየሄድን ነው ማለት ይቻላል።

ሙሴ ከፈርዖን ጋር ያደረገው ክርክር አንድ መሪ ከአቋሙ እንዲያፈገፍግ ስለሚገጥመው የመደራደር ፈተና ዓይነተኛ ምሳሌ ሊሆነን ይችላል። እግዚአብሔርን እንዲያመልኩ እስራኤልን ከግብጽ ለማውጣት የነበረውን የማያወላውል አቋም ሲረዳ ዓላማውን ለማጨናገፍ ፈርዖን የሚቻለውን አማራጭ አሳብ ሁሉ አቅርቦአል። የመጀመሪያው መደራደሪያ አሳብ «ደስ በሚያሰኛችሁ መንገድ እግዚአብሔርን አምልኩ፤ ይሁን እንጂ እርሱን ለማምለክ የግድ ከግብጽ ምድር መውጣት የለባችሁም፤ እዚሁ ልታመልኩት ትችላላችሁ» የሚል ነበር። ይህን አባባል በዘመናችን አስተሳሰብ ስንመለከተው። «ሃይማኖታችሁን በግላችሁ ያዙ፤ ሆኖም አመለካከታችሁ ጠባብ መሆን የለበትም፤ ከዓለም ጋር ያላችሁን ግንኙነት ሙሉ በሙሉ ማቋረጥ ተገቢ አይደለም» የሚል ሆኖ እናገኘዋለን።

ያቀረበው አሳብ ተቀባይነት ማጣቱን ሲረዳ ፈርዖን «እግዚአብሔርን ለማምለክ የግድ ከግብጽ አገር መውጣት አለብን የምትሉ ከሆነ

እንደዚያ ማድረግ ትችላላችሁ፤ ሆኖም ርቃችሁ አትሂዱ» የሚል ሌላ ድርድር ይዞ ቀረበ። በዚህ በምንኖርበት ዘመንም እንዲሁ «ሃይማኖት ጥሩ ነው፤ ነገር ግን አክራሪዎች መሆን የለባችሁም፤ ከዓለማዊ ነገሮችም ይህን ያህል መራቅ የለባችሁም» የሚል ድርድር ከየአቅጣጫው ይሰነዘራል።

ቀጥሎ ያቀረበው ደግሞ ሀዘኔታና ተቈርቋሪነትን የሚያሳይ ዓይነት ነበር፤ «እናንተ ወንዶቹ ሄዳችሁ አምልኩ፤ ሴቶቹና ሕፃናቱ ግን እዚሁ ይቅሩ»። በሌላ መልኩ ስንመለከተው «እናንተ ብትፈልጉ ከዓለማዊ ነገሮች መቆራረጥ ትችላላችሁ፤ ሆኖም በጣም ግትር በመሆን ቤተሰባችሁንም ጭምር ከዚህ ዓለም ሥልጣኔና ጣፋጭነት ማቆራረጥ ተገቢ አይደለም» እንደ ማለት ነው።

በመጨረሻ ያቀረበው አማራጭ ደግሞ ለቁሳዊ ነገሮች ያላቸውን ፍቅርና ፍላጎት የሚፈታተን ነበር፤ «ከፊሊጋችሁ እናንተ ሂዱ፤ እንስሶቻችሁንና ንብረታችሁን ግን በግብጽ ትታችሁ ሂዱ።» ይህም ቢሆን «በሃይማኖታችሁ ምክንያት ያፈራችሁትን ሀብትና ጥሪት ማጣት ተገቢ አይደለም።» የሚል ከሰው ልጅ ሀብትና ንብረት ወዳድነት ጋር የተያያዘ አደገኛ ድርድር ነው።

ግልጽና ጥርት ያለ መንፈሳዊ እይታ ስለ ነበረው ሙሴ የሰጠው መልስ አጭርና ቁርጥ ያለ ነበር፤ «ከእነርሱ አንድ ሰኮናም አይቀርም» ነበር ያለው። (ዘጸ. 8:25፣ 28፣ 10:11፣ 24፣ 26)። ስለሆነም ሙሴ እንደ መሪ የቀረበለትን የመጀመሪያ ከባድ ፈተና አልፎአል ማለት ነው።

ታዋቂ የመሆን ፍላጎት

እንደ ሌሎች ታላላቅ መሪዎች ሁሉ ሙሴም ታዋቂ በመሆን ምኞት ተፈትኖአል። ሙሴ ብቻውን ከእግዚአብሔር ጋር በተራራው በነበረ ጊዜ እስራኤል ጣዖት ማምለክ ጀመሩ፤ በዚህም እግዚአብሔር በጣም ተቈጣ። «ከርስታቸው አጠፋቸው ዘንድ በቸነፈር እመታቸዋለሁ፤ አንተንም ለሚበዛና ለሚጠነክር ሕዝብ አደርግሃለሁ» በማለትም ሙሴን ተናገረው (ዘጸ. 14:12)። የእስራኤል አለማመንና በየጊዜው ማጉረምረም ለሙሴ ትልቅ ፈተና ነበር፤ ስለሆነም እግዚአብሔር ያቀረበው አሳብ ከሸክሙ የሚገላግለውና የተሻለ ኑሮን ለመኖር የሚያስችለው መስሎ ቢታየው አይፈረድበትም ነበር።

በመጀመሪያ ደረጃ፣ አሳቡን ያቀረበው እግዚአብሔር ራሱ እንደመሆኑ መጠን ፈተናው ቀላል አልነበረም፤ ውሳኔ ላይ ከመድረሱ በፊት ብዙ ማውጣት ማውረድ ነበረበት። ይሁን እንጂ፣ እግዚአብሔር ላቀረበው አሳብ ሙሴ የሰጠው መልስ ከምንም ነገር ይልቅ ራስ ወዳድ

አለመሆኑን ይመሰክርለታል። የእርሱ ትልቁ አሳብ የእግዚአብሔር ክብርና የሕዝቡ ጥቅም ነበር። ራሱን ከፍ ከፍ የማድረግና ታዋቂ የመሆን አሳብ በልቡ ውስጥ ምንም ስፍራ አልነበረውም። ከዚህ ይልቅ እግዚአብሔር ሕዝቡን እንዳያጠፋ ማለደ፣ በዚህም ምክንያት ሊመጣ የነበረው እልቂት ተመለሰ።

የማይቻል የሚመስል ሁኔታ

አንድ ታዋቂ ሰው መሪ ለመሆን በእጩነት ለሚቀርቡ ሰዎች «ለመሆኑ፣ የማይቻል የሚመስል ሁኔታ ሲገጥምህ ምን ታደርጋለህ?» በማለት የመጠየቅ ልማድ ነበራቸው። እኚህ ሰው መሪዎች ከቀላሉ ይልቅ ከባዱን ሥራ እንዲጋፈጡ ያበረታቱ ነበር፤ ምክንያቱም አቅምና ጉልበታቸውን በሙሉ የሚጠይቅ፣ በእግዚአብሔር እንዲደገፉና የሌሎችንም እገዛ እንዲጠይቁ የሚያደርጋቸው እንዲህ ያለው ከባድ የሥራ ኀላፊነት እንደሆነ ስለሚያውቁ ነው። «ለጥቃቅን ነገሮች ትኩረት አልሰጥም፤ ምክንያቱም ሌሎች ሊሠሩዋቸው ይችላሉና» የሚል አባባልም ነበራቸው። የአገልጋይ ማንነት የሚለካውና የሚመዘነው አስቸጋሪ ሁኔታዎች ሲገጥሙት ነው።

በዓለም ታሪክ እንደዚህ እንዳለንበት ዘመን የመሪዎችን ችሎታ የሚፈትን ችግር የታየበት ወቅት በፍጹም አልታየም ብንል ማጋነን አይሆንም። መፍትሔ የሚያሻቸው ብዙ ችግሮች ተከስተዋል፤ ከዚህ በፊት ያልነበሩ የተሰያዩ አደጋዎች ተጋርጠዋል። አንዳንዶቹም ጨርሶ መፍትሔ የማይገኝላቸው የሚመስሉ ናቸው። የመሪዎች ብርታትና መፍትሔ የማቅረብ ችሎታ የሚታየው በዚህ ጊዜ ነው። እስራኤል ቀይ ባሕር ሲደርሱ ሙሴን አስቸጋሪ ሁኔታ ገጥሞት ነበር። ፊት ለፊቱ ቀይ ባሕር ነበር፤ ከኋላው የፈርዖን ሠራዊት ነበር፤ ግራና ቀኙንም መታለፍ የማይችል ተራራና ጭው ያለ በረሃ ነበር። በዚህ ጊዜ የሕዝቡ ልብ ቀለጠ፤ ብርታትና ወኔው ሁሉ ወደቀ። «በዚህ ምድረ በዳ እንድናልቅ ያመጣኸን ከግብጽ አገር መቃብር ስለሌለ ነው?» በማለት ሙሴ ላይ አጉረመረሙ። የእምነት ሰው ሙሴ ግን ልቡን በእግዚአብሔር ላይ አሳረፈ። በዚያ ቀን ሙሴ የሰጠው መመሪያ ሞራላቸው ለወደቀው እስራኤላውያን በፍጹም የማይመስል ነበር። እርሱ ግን እውነተኛ መሪነቱን ለማስመስከር አጋጣሚው ምቹ ሆኖለታል።

«አትፍሩ» አለ ሙሴ ድምፁን ከፍ አድርጎ። እንደ እውነቱ ከሆነ ግን እንዳይፈሩ የሚያደርጋቸው ምንም ምክንያት አልነበረም።

«ተረጋግታችሁ ቁሙ!» አለ። እየገሠገሠ ባለው የፊርያን ሠራዊት ፊት ተረጋግቶ መቆም ማለት ሞት እንጂ ሌላ ምንም ሊሆን አይችልም።

«የእግዚአብሔርን ማዳን እዩ» አለ። በሰው ዓይን ግን የእግዚአብሔርን ማዳን የሚያዩበት ሁኔታ ላይ አልነበሩም (ዘጸ. 14:11-13)።

በዚያ የማይቻል በሚመስል ሁኔታ ውስጥ ሙሴ የእምነትን ዓዋጅ ዐወጀ፤ ያለ አንዳች መናወጥ በእግዚአብሔር ጸና፤ ስለዚህም ብዙ ጊዜ መሪዎች የሚገጥማቸውን ፈተና በከፍተኛ ውጤት ማለፍ ቻለ። እግዚአብሔርም አከበረው። «ዛሬ የምታዩዋቸውን ግብፃውያንን ለዘላለም አታዩዋቸውም» በማለት የተናገረው ትንቢት በትክክል ተፈጸመ። የእግዚአብሔርን ማዳንና የግብፃውያንን ጥፋት በዓይናቸው አዩ። ከዚህ የምንማረው እግዚአብሔር ሕዝቡን ወደ አስቸጋሪ ሁኔታ ቢያመጣቸው እንኳ እምነታቸውን በእርሱ ላይ ካደረጉ አስደናቂ ኃይሉን በመግለጥ እንደሚታደጋቸው ነው።

ቻይናን በወንጌል ለመድረስ ታጥቆ የተነሣው ሐድሰን ቴለር ብዙ ጊዜ እንዲህ ያሉ ከባድ ችግሮች ይገጥሙት ነበር። በኋላ ግን ያሳለፈውን ልምምድ መሠረት በማድረግ ሲናገር «ታላላቅ ሥራዎች ሁሉ ሦስት ገጽታዎች አሉዋቸው፤ በመጀመሪያ የማይቻል ይመስለናል፤ ሥራውን በመሥራት ላይ እያለን እንዴት ከባድና አስቸጋሪ ነው እንላለን፤ በእምነት ወደፊት እየገፋን ስንሄድ ግን «እፎይ» ሥራው ተሠርቶአል የምንልበት ደረጃ ላይ እንደርሳለን» ብሎአል። አስቸጋሪ ሁኔታዎችን አስመልክቶ አንድ ሌላ ሰው ደግሞ በሚከተለው መልኩ ተናግሮአል

> እንደ ቀይ ባሕር ያለ ችግር ፊት ለፊታችሁ ተጋርጦ ይሆን? እንግዲያውስ ተሻግራችሁ ማለፍ እንጂ ሌላ መውጫ መንገድ የላችሁም። የከበባችሁ የፍርሃት ጨለማ እስኪወገድ ያ መናወጥ እግዚአብሔርን በማመን ጠብቁ። ያኔ ነፋሱን ያዝዛል፤ ባሕሩን እንደ ክምር ያደርገዋል፤ ለነፍሳችሁም «አሁን ማለፍ ትችያለሽ» ይላታል። ጠላት እንዳያገኛችሁ፤ ባሕሩም እንዳያሰጥማችሁ በእጁ ይጋርዳችኋል። የጠላት ሠራዊት ይሰጥማል፤ እናንተን ግን እንደ መንገድ በባሕሩ ውስጥ ያሳልፋችኋል። መከራው ሲያልፍ የምታዩት ጌታን ብቻ ይሆናል። ወደ ክብር ቦታ ስለምትደርሱም በዝማሬ እርሱ ታመሰግናላችሁ።

ውድቀት

ሥራቸው ያለምንም ችግር የተከናወነላቸው የሚመስሉ ሰዎችን ሕይወት ቀረብ ብለን ብንመረምር ምናልባት ሳንገረም አንቀርም። የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያዎችን በማዘጋጀት የታወቀ አንድ ታላቅ ምሑር ብዙ ሕዝብ በተሰበሰበበት አዳራሽ ንግግር ካደረገ በኋላ «ከእንግዲህ ወዲህ በእንዲህ ዓይነቱ ስብሰባ ምንም ንግግር አላደርግም» በማለት ብቁ አለመሆኑን ቢናገርም፤ ሕዝቡ ግን በትምህርቱ ተገርከው ወደየቤታቸው እየሄዱ ነበር። ታላላቅ ተግባራትን ካከናወንን በኋላ እንዲህ ያለ ውድቀትና ተስፋ የመቁረጥ ስሜት ሊኖር እንደሚችል ማወቅ አለብን። ምን ጊዜም እኛን ከማጥቃት የማይተኛው ጠላት የሚሠራውን ተንኮል መዘንጋትም አይኖርብንም።

አንድ መሪ የራሱን ውድቀት የሚቀበልበት ሁኔታ ለወደፊት አገልግሎቱ ከፍተኛ እገዛ ሊያደርግለት ይችላል። ምናልባትም አንዳንዶቻችን ኢየሱስ ተላልፎ በተሰጠ ጊዜ ጴጥሮስ የደረሰበት ውድቀት በእግዚአብሔር መንግሥት የነበረውን የመሪነት ስፍራ ለዘላለም አሳጥቶታል ብለን እናስብ ይሆናል። ይሁን እንጂ የጌስሐው ጥልቀትና ለኢየሱስ የነበረው ፍቅር እውነተኛነት ሰፊ የአገልግሎት በር እንደከፈተለት እንመለከታለን።

የመጽሐፍ ቅዱስ ታላላቅ ሰዎችን ሕይወት ብናጠና አንዳንዶቹ ውድቀት ደርሶባቸው እንደነበር እናያለን፤ የአንዳንዶቹ ውድቀት በጣም ከፍተኛ ነበር፤ ይሁን እንጂ ከወደቁበት ተነሡ እንጂ ወድቀው አልቀሩም። ውድቀታቸውና በዚህም ምክንያት ያደረጉት ንስሐ የእግዚአብሔርን ጸጋ ስፋትና ጥልቀት ይበልጥ እንዲረዱ አድርጎአቸዋል። ለወደቁ ልጆቹ ሌላ ተጨማሪ ዕድል የሚሰጥ አምላክ መሆኑንም ተምረዋል።

አንድ የታሪክ ምሑር ሲጽፍ፡ «የሰው ዋጋው የሚለካው በሕይወቱ እንጂ በውድቀቱ አይደለም። ጌታን እንደሚክድ ማስጠንቀቂያ ቢሰጠውም ሐዋርያው ጴጥሮስ በመጀመሪያው ፈተና ሦስቴ ክዶታል። ይሁን እንጂ ብርታቱንና ድካሙን የሚያውቅ ጌታ ለክፍተኛ አገልግሎት መርጦታል» አለ።

የተሳካለት መሪ ውድቀት የመጨረሻው አለመሆኑን ያውቃል፤ ጥፋቱ የእርሱ ይሁን ወይም የሌሎች ግምት ውስጥ ሳያስገባ ጉዞውን ይቀጥላል። ባለበት መልኩ ሐቅን ስለሚቀበል ሁልጊዜ ትክክል ሊሆን እንደማይችል ይገነዘባል። ምንም ውድቀት የማይገጥመው መሪ እንደሌለ ስለሚያውቅ ተስፋ አይቆርጥም።

ቅናት ወይም ምቀኝነት

አንዳንድ ጊዜ የእርሱን ስፍራ መያዝ የሚፈልጉ በቅናት ወይም በምቀኝነት የተነሣሡ ሰዎች መሪው ላይ ችግር ሊፈጥሩበት እንደሚችሉ መታወቅ አለበት። በአገልግሎቱ እያደገና ተሰሚነቱም እየጨመረ ሲሄድ ሙሴን የመሰለ ታላቅ መሪ እንኳ ከዚህ ችግር አላመለጠም። ማጉረምረምና ስፍራን አለማወቅ ብዙውን ጊዜ ጠላት የሚጠቀምበት መሣሪያ ነው።

ከዚህ አኳያ ሙሴ ላይ የመጀመሪያውን ችግር የፈጠሩበት የራሱ ወንድምና እህት ነበሩ። ሙሴ ራሱን በመካድ የቀረበለትን መለኮታዊ ጥሪ ባይቀበል ኖሮ፣ አሁንም በግብጽ በከባድ ሥራ እየማቀቁ ይኖሩ እንደነበር የዘነጉ ይመስላል። እርሱ ያን መሥዋዕትነት ባይከፍል ኖሮ የግብፁውያን ባሪያዎች ሆነው ይቀሩ እንደነበር ዘንግተዋል።

በዚያ ጊዜ ማርያም በዕድሜ የገፋች ሴት ስለነበረች ምቀኝነት ምን ያህል መጥፎ እንደሆነ ከእግዚአብሔር ጋር ባሳለፈችው ልምምድ ማወቅ ነበረባት። ይሁን እንጂ ኢትዮጵያዊቱን ሴት ማግባቱን እንደ ሰበብ ተጠቅማ በሙሴ ሥልጣን ላይ የሐሜት ዘመቻ ጀመረች። ዘርን መሠረት ያደረገ ጥላቻ ዛሬ የተጀመረ አይደለም፤ በዚህች የሴላ አገር ሴት መበለጥን መቀበል አልፈለገችም፤ ደካማው አሮንንም የዓመፅዋ ተባባሪ እንዲሆን ተጠቀመችበት።

ማርያምና አሮን የሙሴ ምክትል በመሆን ብቻ የሚመለሱ አልነበሩም፤ ይልቁንም እርሱን ከኀላፊነት ለማውረድና በሕዝቡ ዘንድ የነበረውን ተቀባይነት ለማሳጣት ሙከራ እንዲያደርጉ ሰይጣን ሊጠቀምባቸው እንመለከታለን። ለእግዚአብሔር ክብር የተቆረቆሩ በሚመስል መልኩ ምቀኝነታቸውን መንፈሳዊ ሽፋን ሊሰጡት ሞክረዋል። «ለመሆኑ እግዚአብሔር የሚናገረው በሙሴ በኩል ብቻ ነው? በእኛ በኩልስ ለሕዝቡ ተናግሮ የለ?» የሚል ጥያቄ በማቅረብ በወቅቱ ብቸኛ የእግዚአብሔር ነቢይ የመሆን መብቱን ተጋፉ።

በዚህ ጊዜ ሙሴ ያደረገው ምሳሌ ሊሆን የሚችል ነው። ምንም እንኳ ጉዳዩ ልቡን ቢያቆስለውም የራሱን ትክክለኛነት ለማሳየት ክርክር መግጠምን አልፈለገም፤ ምክንያቱም የእርሱ ዋናው ናፍቆት የእግዚአብሔር ክብር እንጂ የራሱ መብትና ዝና አልነበረም። ምን ያህል ትሑት እንደነበረ የተመሰከረለትም ከዚህ ጋር በተያያዘ ነበር። «ሙሴም በምድር ላይ ካሉት ሰዎች ሁሉ ይልቅ እጅግ ትሑት ሰው ነበረ» (ዘኁ. 12:3)። ሙሴ በዝምታ ማለፍ ቢፈልግም፤ እግዚአብሔር

ግን በባርያው ሥልጣን ላይ የተቃጣውን ዓመፅ በቸልታ ማለፍ አልፈለገም።

ዓመፁ ሕዝቡን ያሳተፈ እንደ መሆኑ መጠን፣ ቅጣቱም በአደባባይና በሕዝብ ፊት መፈጸም ነበረበት። «እነሆም ማርያም ለምጻም ሆነች፤ እንደ አመዳይም ነጭ ሆነች» ይላል ቃሉ ስለ ደረሰባት ፍርድ ሲያመለክት። ምንም እንኳ ድካምና ጉድለት ቢኖርባቸውም እርሱ የቀባቸውን አገልጋዮች መንካት የሚያስከትለውን ፍርድ ማርያም ላይ ከደረሰው መረዳት ይቻላል። ሰዎች ሊያደበዝዙት ቢሞክሩም የሙሴ ታላቅነት እንደገና በገሃድ ታየ። በደል ላደረሰችበት እህቱ መጸለይና መማለድ ጀመረ፤ እግዚአብሔርም ጸሎቱን ሰምቶ ምሕረት አደረገላት።

መንፈሳዊው መሪ ከዚህ የሚማረው ግልጽ ነው። የሾመው እግዚአብሔር ራሱ መሆኑን እስከተቀበለ ድረስ፣ ምቀኞች ለሚያስወሩት አሉባልታ መልስ መስጠትና ትክክለኛነቱን ለማሳየት ሙከራ ማድረግ የለበትም። ጠበቃና ተሟጋች በሚሆንለት ጌታ እጅ ስለሆነ ልቡ ማረፍ አለበት፤ እግዚአብሔር ለማርያም የሰነዘረው ተግሣጽም ይህንኑ ነው የሚያረጋግጠው። «በባሪያዬ በሙሴ ላይ ትናገሩ ዘንድ ስለምን አልፈራችሁኝም?» (ዘኁ. 12:8)። ሁለተኛው ተቃውሞ የተነሣው ደግሞ በቆሬና አብረውት በነበሩ ሰዎች አማካይነት ሲሆን፣ ያለ ምንም በቂ ምክንያት በሙሴና በአሮን ላይ በምቀኝነት ተነሣሥተዋል። ለምንድን ነው እነርሱ ብቻ ተሰሚነትና ተቀባይነት የሚኖራቸው? ለመሆኑ ከእኛ መሐል የእነርሱን ያህል ችሎታና ዕውቀት ያለው ሰው ጠፍቶ ነው? ከእግዚአብሔር መልእክትን ተቀብሎ ለሕዝቡ የማስተላለፍ ብቃት ያላቸው ሙሴና አሮን ብቻ ናቸው? ምቀኝነታቸውን ሃይማኖታዊ መልክ ለመስጠት እንዲያመቻቸውም፦ «ምነው ከልክ አላለፋችሁም! የማኅበረ ሰቡ አባላት ሁሉ እያንዳንዳቸው የተቀደሱ ናቸው፤ እግዚአብሔርም ከእነርሱ ጋር ነው ታዲያ በእግዚአብሔር ማኅበር ላይ የምትታበዩት ለምንድን ነው?» አሉ (ዘኁ. 16:3)።

አሁንም ቢሆን ሙሴ ስለ ራሱ አልተከራከረም፤ ሆኖም እግዚአብሔር እነዚያን ምቀኞች በዋዛ አልተዋቸውም፤ የሚገባቸውን ፍርድ ሰጣቸው። ፍርሃት በሕዝቡ ላይ ወደቀ፤ የሙሴ ትልቅነትና ዝና ከበፊቱ ይልቅ ገነነ።

እርሱ የጠራቸው መሪዎች ላይ በሚቃጣ አድማ እግዚአብሔር ቀናተኛ ነው። ያከብራቸዋል፤ ይጠብቃቸዋል፤ ጽድቃቸውን ገሃድ ያወጣል፤ እነርሱ ለመብትና ክብራቸው መቆርቆር እንደሌለባቸውም ያሳያቸዋል።

18

አገልግሎትን ለሌሎች የማካፈል ጥበብ

ሙሴም ከእስራኤል ሁሉ አዋቂዎችን መረጠ፡... በሕዝቡም ላይ አለቆች አድርጎ ሾማቸው.... የከበደባቸውንም ነገር ወደ ሙሴ አመጡ፤ ታናሹን ነገር ሁሉ ግን እነርሱ ፈረዱ።

ዘጸአት 18:25-26

መሪነት ለሚለው ቃል ከሚሰጡ ትርጉሞች አንዱ «የሌሎችን ስጦታና አቅም በመገንዘብ እያንዳንዱን ሰው በተገቢው ኀላፊነት ስፍራ የማስቀመጥ ችሎታ» ይላል። እርሱ ብቻ መሥራቱ ሳይሆን ሥራው በሌሎችም ጭምር እንደሠራ የሚያደርግ መሪ በእርግጥም የተሳካለትና የተዋጣለት ነው ማለት ይቻላል። ዲ.ኤል ሙዲ የተባለው የወንጌል ሰባኪ ሲናገር «የሺህ ሰዎችን ሥራ ከመሥራት ይልቅ፤ ሥራው በሺህ ሰዎች እንዲሠራ ማድረግን እመርጣለሁ» ይል ነበር። ትክክለኛ ሰዎችን መምረጥና ለእያንዳንዱ የሚመጥነውን የሥራ ድርሻ መስጠት መቻል የእውነተኛ መሪ ባሕርይ ነው። ቻይናን በወንጌል ለመድረስ የተመሠረተው ግዙፍ ሚስዮናዊ ድርጅት ዳይሬክተር የነበሩ ሰው ሲናገሩ፡- «የሰዎችን ችሎታ ማድነቅና በችሎታቸው መጠን መሥራት የሚችሉትን የሥራ ድርሻ ማከፋፈል ራሱን የቻለ ስጦታ ነው፤ በተለይም ደግሞ የእኛን ዓይነት ሥራ ለሚሠራ ድርጅት ይህ እጅግ አስፈላጊ ነው» ብለዋል።

መሪው ይህን ካደረገ ጉልበትና ጊዜውን በማያስፈልግ ሁኔታ ከማባከን ይድናል፤ ሥራውም የተሳካና ያማረ ይሆናል።

ሰዎች ላይ የኀላፊነትን ሸክም ስንጫን ከዚያ ጋር አብሮ ሥልጣኑንም ልንሰጣቸው ይገባል። ይሁን እንጂ፤ ሥልጣኑን ለሌሎች ማጋራት የማይፈልግ መሪ የሥራ ድርሻን እንጂ ሥልጣኑን ማካፈል ደስ አይለውም። ሥራውን ሊሰጣቸው ይችላል፤ ኀላፊነትና ሥልጣን ግን በእርሱ ብቻ እንዲወሰን ይፈልጋል። ይህ አብረውት የሚሠሩ ሰዎችን ሊያስከፋቸው ይችላል፤ ሥራው ውጤታማ እንዳይሆንም እንቅፋት ይሆናል፤ ከዚህም በላይ እነርሱ ላይ እምነት እንደሌለው ተደርጎ ሊተረጎም ስለሚችል ከሙሉ ልባቸው አይሠሩም። እርግጥ ነው፤ ሥራውን የተረከበው ሰው ከእርሱ በላይ ያለውን ሰው ያህል በሚገባ ላይሠራው ይችል ይሆናል፤ ይሁን እንጂ ከልምድ እንደታየው ከሆነ ዘወትር እንዲህ ይሆናል ማለት አይደለም። ዕድሉ ከተሰጣቸው ወጣቶቹ ከሽማግሌዎቹ ይልቅ የዘመኑን አስተሳሰብ ስለሚያውቁ

በተሻለ ሁኔታ ሊሠሩ ይችላሉ። በዚህም ይሁን በዚያ የሥራ ድርሻውና ሥልጣኑ በአንድነት ካልተሰጠው በቀር አንድ ሰው ከልምድ እንዴት ሊማር ይችላል?

«አንድ መሪ የተሳካለትና የተዋጣለት ሊሆን የሚችለው የሥራ ድርሻን ለሌሎች በሚያካፍልበት መጠን ነው።» ብቻውን የሚሸከመው ኀላፊነት የሥራ ጫናውን ከማክበዱ ሌላ ለሥራው መሳካት አስተዋፅዖ አይኖረውም። አንዳንድ መሪዎች አብረዋቸው የሚሠሩ በሳልና አስተዋይ ሰዎች ሥልጣናቸውን እንዳይወስዱባቸው ወይም ከእነርሱ የበለጡ መሆናቸው እንዳይታይ ይፈራሉ፤ ስለሆነም በተቻለ መጠን ሥራ እንኺ ኀላፊነትን አይሰጡዋቸውም።

መሪው የሥራ ድርሻን ለተገቢው ሰው ማካፈል ካልቻለ በራሱ ላይ የማያስፈልግ ሸክም ከመጫኑም በላይ ጊዜና ጉልበቱን በየጥቃቅኑ ጉዳይ ያባክናል፤ ከዚህም የተነሣ ዋነኛ ኀላፊነቱን እንኳ በሚገባ መፈጸም ያቅተዋል። ከእርሱ ጋር የሚሠሩ ሰዎች እምቅ ችሎታም ወጥቶ እንዳይታይ መሰናክል ይሆናል። እኔ ካልሠራሁበት በቀር ሥራው ይበላሻል ብሎ የሚያስብ ሰው የአስተሳሰብ ጠባብነቱን ብቻ ሳይሆን ምን ያህል ትምክህተኛ መሆኑንም እያሳየ ነው። የተለያዩ ሥራዎችን ለሌሎች ካካፈለ በኋላ በራሱ ሥራ ድርሻ ላይ ብቻ ትኩረት የሚያደርግ መሪ ግን ውጤታማ ሊሆን ይታያል።

አንዱ ሥራውን ወይም ውክልናውን ከሰጣቸው በኋላ በእነርሱ ላይ እምነት ሊኖረውና ይህንንም ሊገልጥላቸው ይገባል። የተሰጣቸውን ኀላፊነት በአግባቡ መወጣት እንዲችሉ ነጻነት መስጠት ይኖርበታል፤ በየጊዜው በሥራቸው ጣልቃ እየገባ ማደናቀፍ የለበትም።

ምናልባትም ሥራውን በአግባቡ ሳያከናውኑ ቢቀሩ እንኳ መጀመሪያውኑ ለዚያ ኀላፊነት የመረጣቸው እርሱ በመሆኑ ችግሩ የእርሱ መሆኑን መቀበል ይኖርበታል። በተሰጣቸው ኀላፊነት ክልል ውስጥ እስከሆኑ ድረስ ውጤቱ ምንም ይሁን ምን የመሪያቸው ድጋፍና እገዛ እንደማይለያቸው የበታች ሠራተኞች እርግጠኛ መሆን ይኖርባቸዋል። የሠራተኞቹ ድርሻ ምን እንደሆኑ በግልጽ ሊነገራቸውና ምንም ዓይነት አለመግባባት እንዳይፈጠር በጽሑፍ መስፈር ይኖርበታል። የዚህ ዓይነት አሠራር ባለ መኖሩ ግን ግባቸው መምታት የነበረባቸው እቅዶች ያለ ፍሬ ቀርተዋል።

በሚስዮናዊነት ሥራ ከትውልድ አገራቸው ውጪ ያገለግሉ የነበሩ ሰው የቅርብ አለቃቸውን በተመለከተ ሲናገሩ፡

> «በሥራ መስክ ባሳለፍኩዋቸው አሥር ዓመታት ትልቁ ደስታዬ ምን ጊዜም የእርሱ ድጋፍና እገዛ እንደማይለየኝ ማወቄ

ነው። በእኔ ላይ ያለው እምነትም ያበረታታኛል። ስለሆነም ከእኔ በሚጠበቅብኝ መሠረት ለተሰጠኝ ሥራ ብቁ ሆኜ እንድገኝ የሚቻለኝን ሁሉ አደርጋለሁ» ብለዋል። ለአለቆቻችን የዚህ ዓይነት ምስክርነት መስጠት የምንደፍር ስንቶቻችን ነን?

ኀላፊነትን ወይም የሥራ ድርሻን ለሌሎች ማካፈልን በተመለከተ ዮቶር ለሙሴ የሰጠው ምክር በመሪነት ስፍራ ላይ ያለን ሁሉ ልንከተለው የሚገባን ነው፤ ይህንንም ከዘጸአት 18፡1-27 መመልከት ይቻላል።

እዚህና እዚያ ተበታትነው በባርነት ያገለግሉ የነበሩ እስራኤላውያን ራሱን የቻለ ሕዝብ ለመሆን እየተደራጁ የነበሩበት ጊዜ ነበር። ይህን ሕዝብ ለማደራጀትና ለመምራት ሙሴ ብቻውን ከጥዋት አንሥቶ እስከ ማታ ድረስ ሲደክም ዮቶር ተመልክቶአል። አዳዲስ ችግሮች እየተከሰቱ ነበር፤ ሙሴ ደግሞ ችግሮችን ለመፍታት ብቻውን እየሠራ ነበር። ሕግ ማውጣቱም ሆነ ሕጉን ማስፈጸሙ የሙሴ ግዴታ ነበር።

በዚህ መልክ ብቻውን ያንን ሁሉ ኀላፊነት መወጣት እንደማይሆንለት የተመለከተው ዮቶር የሥራ ድርሻን ለሌሎች ማካፈልን በተመለከተ ሁለት ጠቃሚ ምክሮችን ሰጠው። በመጀመሪያ ደረጃ፣ «ሥራው ብዙ ስለሆነ ይደክምሃል፤ አንተ ብቻህን ልትሠራው አትችልም» አለው (ቁ. 18)። አንድ ሰው ብቻውን የሚያከናውነው የጉልበትም ሆነ የአእምሮ ሥራ ውሱን ነው፤ ከዚያ ካለፈ ግን ችግር ይከተላል። በሁለተኛ ደረጃ፣ ሥራው በአስፈላጊ ጊዜና ቅልጥፍና እየተከናወነ አልነበረም፤ ጉዳያቸው ቶሎ እልባት ባለማግኘቱ ሰዎች እያማረሩ ነበር። ስለሆነም ኀላፊነቱን ለሌሎች ማካፈሉ ውሳኔ የሚያሻቸውን ጉዳዮች ሂደት ያፋጥናል፤ ሕዝቡም የሚያማርሩበት ምክንያት አይኖራቸውም (ቁ. 23)።

ከዚያ በኋላ ደግሞ ዮቶር ሁለት የመፍትሔ አሳቦችን አቀረበ። ሙሴ የእግዚአብሔር ተጠሪ እንደመሆኑ መጠን መንፈሳዊ ነገሮችን ማስተማርና ለሕዝቡ መመሪያ ማውጣት የእርሱ ሥራ ድርሻ ይሆናል፤ ከአቅሙ በላይ የሆነ ችግር ሲገጥመው ከእግዚአብሔር መመሪያ ማግኘት ያለበትም እርሱ ነው (ቁ. 16፣ 19-20)። ከዚያ በታች ያሉትን ማለት መመሪያዎችን የማስፈጸም ኀላፊነቱን ግን ብቁ ለሆኑ ሰዎች ማካፈል ይኖርበታል፤ ያኔ የማያስፈልግ ሽክምን ከትከሻው ማውረድ ይችላል። ምክሩ በጣም ጠቃሚ ውጤት አስገኝቶአል። ሙሴ ብቻውን ኀላፊነቱን ለመወጣት ቢፈልግ ኖሮ ከእርሱ በኋላ ሕዝቡን መምራት የሚችሉ ሰዎችን ማግኘት አይቻልም ነበር። በጥቂት በጥቂቱ ኀላፊነትን መወጣትና በኋላም ሕዝቡን

ለመምራት ብቃት ያላቸው መሪዎችን ማግኘት አይቻልም ነበር። ተስፋ ተጥሎባቸው የነበሩ የእግዚአብሔር ሥራዎች ያለ ፍሬ የቀሩት መሪነት ላይ ያሉ ሰዎች በጊዜው የሚተኳቸውን ሰዎች ባለማሠልጠናቸው ነው።

ዮቶር የሰጠውን ምክር በመቀበሉ ሙሴ ብዙ ተጠቅሞአል። ዐቢይ ለሆኑ ጉዳዮች ትኩረት ለመስጠት በቂ ጊዜ አገኘ። ከእርሱ በታች ሆነው የሚሠሩ ሰዎችም አቅምና ችሎታቸውን የሚያስመሰክሩበት ዕድል አገኙ። ከዚያ በፊት ግን ይህ ችሎታ ሊኖራቸው እንደሚችል ማንም የጠረጠረ አልነበረም። ጎላፊነቱን ብቻውን ቢይዘው ኖሮ ተቃዋሚዎቹ ሊሆኑ የሚችሉ እነዚያ ባለ ስጦታ ሰዎች የተሰጣቸውን ጎላፊነት በሚገባ በመወጣታቸው አጋዥና ደጋፊዎቹ ሆኑ። ለችግሩ አፋጣኝ መልስ በማግኘቱም ሕዝቡ ማማረሩንና መነጫነጩን አቆመ። ይህን እርምጃ በመውሰዱ ሙሴ ከእርሱ ሞት በኋላ ሕዝቡን መምራት የሚችሉ ብቁ ሰዎችን ማፍራት ችሎአል።

«አንተ ይህን ብታደርግና እግዚአብሔርም ይህንኑ ቢያዝዝህ ድካምህን መቋቋም ትችላለህ» በማለት ዮቶር ለአማቹ ለሙሴ የሰጠው ምክር ዘመን የማይሻረው መንፈሳዊ እውነት ነው (ዘጸ. 18:23 አ.መ.ት)። ምክሩ የእርሱ ሳይሆን የእግዚአብሔር መሆኑን ነበር የነገረው። ከዚህ የምንማረው እግዚአብሔር ለመረጠው ሰው አንድን ሥራ ሲሰጠው፣ ከዚያ ጋር አብሮ ሙሉ ጎላፊነትንም ጭምር እንደሚሰጠው ነው። አንዳንድ ሥራዎችን ከእኛ ይልቅ ሌሎች በተሻለ ጥራት ሊሠሩዋቸው ይችላሉ፤ ስለዚህም ለእነርሱ መተው ሥራውን ውጤታማ ያደርገዋል። ምናልባት እንኳ ሥራው ቢበላሽ የተሻለ መመሪያ መስጠት እንጂ ሥራውን ልንነጥቃቸው አይገባም፤ ከሰዎች ፍጽምናን ለሚጠብቅ መሪ ግን ይህ ራሱን የቻለ ፈተና ነው። ከእነዚያ ጎላፊነት ከተሰጣቸው ሰባ ሰዎች ይልቅ ሙሴ ብቻውን ጎላፊነቱን በተሻለ ጥራት ሊወጣ ይችል ነበር ቢባል እንኳ ከሥራው ጫና የተነሣ ያለ ጊዜው ይሞት ነበር።

መሪዎችን በተመለከተ ዮቶር ለሙሴ የሰጠው ምክር መንፈሳዊ ጥበብና ማስተዋልን የሚጠይቅ ነበር። የሚመረጡ ሰዎች ለሥራው በቂ ችሎታ ሊኖራቸው ይገባል። እግዚአብሔርን የሚፈሩና ሰዎችን የሚያከብሩ መንፈሳውያን ሰዎች ሊሆኑ ይገባል። መመለጃን ወይም ጉቦን የማይበሉ ታማኝና የተከበሩ ሰዎች ሊሆኑ ይገባል።

ከዚህም በተጨማሪ መሪዎች ማስተዋል ያለባቸው ሌሎች ጠቃሚ ትምህርቶችም ይኖራሉ። በተገቢ ጥራትና ብቃት መሥራት የማይችሉትን ሥራ መቀበል ስሕተት እንደሆነ መረዳት ይኖርባቸዋል።

ከድርሻችን በላይ ሥራን መሥራት በራሱ ጽድቅ አይደለም። አቅምና ችሎታችን ውሱን መሆኑን መገንዘብ አለብን። እንደ ዮቶር ሆነው በአጠገባችን ያሉ ሰዎች እኛ ከምንረዳው በላይ የሥራው ጫና የሚያስከፍለው ዋጋ ይታያቸዋል፤ ስለዚህም ምክራቸውን መቀበል ይኖርብናል። ሌላው ማስተዋል ያለብን ደግሞ በእግዚአብሔር አገልግሎት እንኳ ቢሆን የተፈጥሮን ሕግ ብንተላለፍ ከቅጣት እንደማናመልጥ ነው። አንዳንድ ጊዜ ከሰዎች ግፊት የተነሣ እግዚአብሔር ያልሰጠንን ሸክም እንሸከማለን። ይሁን እንጂ በእንዲህ ዓይነቱ ሸክም ምክንያት ለሚደርስብን ስብራት እግዚአብሔር ተጠያቂ አይሆንም።

በሌላ አገር የወንጌል መልእክተኛ ሆነን የምናገለግል ሰዎች መሪነት ችሎታ የሚፈተነው ለአገሬው ሰዎች የሥራ ኀላፊነትን በማካፈል ነው፤ እኛ ራሳችን ለዚያ ኀላፊነት የበቃነው አስፈላጊውን ሥልጠና ወስደን ነው፤ ሥራችንን በተመለከተ ሁልጊዜ የተሳካልን እንዳልነበርንም እናውቃለን። ስለዚህም ኀላፊነትን ለሚቀበሉ ሰዎች ተገቢውን ሥልጠና መስጠትና በልምድ የመሪነት ችሎታን እንዲያዳብሩ ዕድል ልንሰጣቸው ይገባል። ያኔ የሰዎች እምቅ ችሎታ ስለሚወጣ ሥራውን በአግባቡ የማከናወን ብቃታቸውንም ያስመሰክራሉ። አላስፈላጊ ክትትል ማድረጉ ግን የሰዎችን በራስ የመተማመን አቅም ያደክማል።

የአንድ ግዙፍ ሚሲዮናዊ ተቋም ዋና ጸሐፊ የነበሩ ሰው ለእያንዳንዱ ሰው ተገቢ የሥራ ድርሻን በማከፋፈል ረገድ ይታወቁ ነበር። ከሥራው ጋር አብረው ሙሉ ኀላፊነትንም ስለሚሰጡዋቸው አላስፈላጊ ክትትል ማድረግ አልነበረባቸውም፤ አብረዋቸው ይሠሩ በነበሩ ሰዎች ብቃትና ችሎታም እምነት ነበራቸው። ይህን በማድረጋቸውም የሚጸጸቱበት ነገር አለመፈጠሩን እኚህ ሰው ተናግረዋል። እርሳቸውን በተመለከተ አንድ ሌላ ሰው ሲናገር- «...በሥራቸው የተዋጣላቸው ሊሆኑ የቻሉት ለእያንዳንዱ ሰው ተገቢ የሥራ ድርሻውን መስጠት በመቻላቸው ነው» ብሎአል።

የሌላ ሚስዮናዊ ተቋም መሪ ባልደረባ የነበረ ሰው ደግሞ ስለ መሪው ችሎታ ሲናገር- «የተዋጣላት መሪ ሊሆን የቻለው የሥራ ክፍፍልን በማድረጉና ለሌሎች በሰጠው ሥራ ጣልቃ በመግባት ባለማደናቀፉ ነው። ቀድሞውኑ የሰዎችን አቅምና ችሎታ ስለሚያውቅ እምነቱን ይጥልባቸው ነበር። ሥራው እንደሚበላሽና ወደ አጉል አቅጣጫ እንደሚያመራ ሲረዳ ግን አስፈላጊውን ማስተካከያ ያደርጋል።» ብሏል።

19

መሪዎችን ስለ መተካት

ባሪያዬ ሙሴ ሞቷል፤ አሁንም አንተና ይህ ሕዝብ ተነሥታችሁ ዮርዳኖስን ተሻገሩ። . . . ከሙሴ ጋር እንደሆንሁ እንዲሁ ከአንተ ጋር አሆናለሁ (ኢያሱ 1:2፣ 5)።

የአንድ እንቅስቃሴ ወይም ሥራ ጽናት የሚለካው መሪው በተለያየ ምክንያት ሥራውን ቢለቅ እንኳ ያለ እርሱ አመራር ሥራው መቀጠል ሲችል ነው። ከሐዋርያት ሥራ 5:38-39 እንደ ምንመለከተው ገማልያል ለፊሪሳውያን የሰጠው ምክር የሚያሳየንም ይህንኑ ሐቅ ነው። «እነዚህን ሰዎች ተዉአቸው፤ አትንኳቸው፤ ሐሳባቸው ወይም አድራጎታቸው ከሰው ከሆነ ይጠፋልና ከእግዚአብሔር ከሆነ ግን ልትገታቸው አትችሉም» አለ ገማልያል የክርስትና እምነት እንቅስቃሴን አስመልክቶ ፊሪሳውያንን ሲመክር (ኢ.መ.ት)። በእግዚአብሔር የተጀመረ፤ በመንፈሳዊ መርሐ ላይ የተመሠረተ ሥራ የመሪዎች ለውጥ ቢኖር እንኳ ከበፊቱ በበለጠ ፍጥነትና እድገት ይቀጥላል እንጂ በፍጹም አይቋረጥም።

አንዳንድ ጊዜ ለእግዚአብሔርና ለሥራው ያለነው ሰዎች እኛ ብቻ እንደሆንን ልናስብ እንችላለን። ኣንደ እውነቱ ከሆነ ግን የአንድ አገልጋይ መሞት እግዚአብሔርን አያስገርመውም፤ ያልተጠበቀ ነገር የሆነ ይመስልም አያደናግጠውም። እኛ ባልጠበቅነው ሁኔታ ታቦቱ ከማደሪያው ሊወሰድ ይችላል ይህ ግን ተስፋ ሊያስቆርጠን አይገባም። አንድ አገልጋይ ቢሞት ወይም ከስፍራው ቢነሣ የተጀመረውን የእግዚአብሔር ሥራ ማን ይመራው ይሆን? በማለት መደናገጥ ኖለብንም። ክርስቲያናዊ የአመራር ስልት ከዓለማዊ አመራር የሚለይባቸው ነጥቦች መኖራቸውን መዘንጋት የለብንም። በመንግሥቱ ውስጥ የመሪነትን ስፍራ እንዲይዙ ሰዎችን የሚመርጠው ራሱ እግዚአብሔር እንጂ ሰዎች አይደሉም (ማር. 10:40)። ዓላማውና እቅዱ እስኪፈጽም ድረስ ለሥራው ተገቢ የሆነ ሰውን ሳያዘጋጅ እቅዱን በጅምር አይተውም።

የታላላቅ እንቅስቃሴ መሥራቾች ሲሞቱ የጀመሩት ሥራ ችግር ላይ ሊወድቅ እንደሚችል እናውቃለን። ይህ እውነት ቢሆን እንኳ የሚፈጠረው ክፍተት ለተጀመረው ሥራ መጥፋት ምክንያት ይሆናል ማለት አይደለም። የአንድ ግዙፍ ሚሲዮናዊ ተቋም ዋና ጸሐፊ በሞቱ

ጊዜ ሥራውም አብሮአቸው ይሞታል ተብሎ ነበር። በኋላ ግን፣ ሌላ ሰው ተተክቶ ውጤታማ በሆነ መልኩ ሥራውን ቀጠለ። እርሱ ሲሞትም እንዲሁ «አሁንስ ሥራው አበቃለት» ተባለ። ይሁን እንጂ ሦስተኛ ሰው በቦታው ተተክቶ መምራት ጀመረ። ታዲያ፣ ይህን ሁሉ የተመለከቱ አንድ ሰው እግዚአብሔር ለጀመረው ሥራ ምን ያህል እንደሚጠነቀቅ መስክረዋል። እኚሁ ሰው ራሳቸው ሲሞቱም በፍጹም ሊተካ የማይቻል ሰው እንደታጣ ነበር የታሰበው፤ ሆኖም በራሱ ጊዜና በራሱ መንገድ እግዚአብሔር አዳዲስ መሪዎችን በማስነሣቱ ሥራው እስከዚህ ጊዜ ድረስ ዘልቆአል። ከዚህ የምንማረው እውነት አንድ ሰው የቱንም ያህል ስጦታ ቢኖረውም፤ የቱንም ያህል ለሥራው የተሰጠ መንፈሳዊ ሰው ቢሆንም፣ በእግዚአብሔር መንግሥት እርሱን የሚተካ አይኖርም ማለት እንደማይቻል ነው።

ሰዎች ባያስተውሉና ባይገነዘቡም እግዚአብሔር ተተኪ መሪዎችን የመምረጥና የማዘጋጀት ሥራውን አላቋረጠም። በአንድ ሰው መነሣት ምክንያት ቀውስ ሲፈጠር እግዚአብሔር የመረጠውን በስፍራው ያስቀምጣል። ይሁን እንጂ፣ በስፍራው ማን መተካት እንዳለበት ማወቅ ይህን ያህል ቀላል አይደለም።

እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ የሰጠው ታላቅ ስጦታ እንደ ሙሴ፣ ዳዊትና ኢሳይያስን የመሳሰሉ የራእይ ሰዎችን እንጂ የተስፋይቱን ምድር አልነበረም ማለት ይቻላል፤ ምክንያቱም ከሁሉ የሚበልጥ የእግዚአብሔር ስጦታ ሰዎች ራሳቸው ናቸው። ለቤተ ክርስቲያን የሰጠው ታላቅ ስጦታም ለመሪነት ያሠለጠናቸው አሥራ ሁለት ሰዎች ነበሩ።

ሙሴ ለመሞት ተቃርቦ በነበረ ጊዜ እርሱን ማን ይተካው ይሆን? የሚል ፍርሃትና ተስፋ መቁረጥ በእስራኤል ሕዝብ ልብ ውስጥ ሳይፈጠር እንዳልቀረ መገመት ይቻላል። ለአርባ ዓመታት ያህል ሕዝቡን ሲመራ ኖሮአል። ችግራቸውን እንዲፈታላቸው፣ በመካከላቸው ለሚነሣው አለመግባባት መፍትሔ እንዲሰጣቸው የሚመጡት ወደ እርሱ ነበር። የእግዚአብሔር ፈቃድ የቱ እንደሆነ የሚያሳያቸውና የሚያስተምራቸው እርሱ ነበር። ስለሆነም ሙሴን የሚተካ ሰው ሊኖር አይችልም በማለት ቢያስቡ የሚገርም አይሆንም። እርግጥ ነው፤ ከእርሱ በታች ሆነው የሚያገለግሉ ሰባ ሰዎች ተመርጠዋል፤ ሆኖም ከእነርሱ አንዱ እንኳ ሙሴን መተካት እንደማይችል ያውቃሉ። በተለይ ደግሞ ሙሴ የሞተው ወደ ተስፋይቱ ምድር ለመግባት በተቃረቡበት፣ ነገሮች ሁሉ በጣም በተወጣጠሩበት ጊዜ መሆኑ ችግሩን ይበልጥ አስከፊ አድርጐታል። ለእንዲህ ዓይነቱ ድንገተኛ ሁኔታ

እግዚአብሔር ሰው ማዘጋጀቱን ማመን በጣም ከብዶአቸው ነበር። እግዚአብሔር ግን የተፈጠረውን ክፍተት የሚተካ ኢያሱን ቀደም ሲል አዘጋጅቶ ነበር። ችግሩና ቀውሱ ለኢያሱ ወደ መድረክ መምጣት ምቹ ሁኔታ ፈጥሮአል።

በታሪክ ውስጥ እንዲህ ያለው ሁኔታ በተደጋጋሚ ታይቶአል፤ እያንዳንዱ ትውልድ መማር ያለበትም ያው ያለፈው ትውልድ የተማረውን ነው። አንድ ታላቅ ወይም ታዋቂ አገልጋይ ቢሞት ወይም በሌላ ምክንያት ከቦታው ቢነሣ እርሱን ማን ይተካው ይሆን? የሚል ፍርሃትና ጥርጥር ይከተላል። ጆን ዌስሊ ሲሞት የሜቶዲስቶች እንቅስቃሴ ዕጣ ፈንታ ምን ይሆን? ተብሎ ነበር። ሳልቬሺን አርሚ የተባለው ግዙፍ ሚሲዮናው እንቅስቃሴ መሥራች ዊልያም ቡዝ ሲሞትም ሥራውን ማን ይመራው ይሆን? የሚል ጥያቄ ተነሥቶ ነበር። በተመሳሳይ ሁኔታ እኛም ብንሆን የቤተ ክርስቲያን መሥራችና መጋቢ ወይም አንድ ታዋቂ ሰው ሲሞት ማን ይተካው ይሆን? በማለት እንጠይቃለን።

በክብር መንገድ የተጓዙ ሰዎች በክብር ወደ መቃብር ይወርዳሉ፤ ሆኖም ሕዝቡን እየመራ በክብር መንገድ የሚሄድ ሌላ መሪ ይነሣል። ታላላቅ መሪዎች በሞት ወይም በሆነ ምክንያት ከስፍራው ሊነሱ ይችላሉ፤ መሪው ብቁና ፍሬያማ የመሆኑን ያህል የእርሱ ከቦታው መታጣት የሚያስከትለው ኪሳራም የዚያኑ ያህል ከባድ ይሆናል። ይሁን እንጂ፣ ወደ ኋላ ዘወር ብለን ነገሮችን ስንመዝን የእነዚያ ሰዎች ከስፍራው መነሣት ሥራውን እንደጠቀመው እንጂ እንዳልጐዳው የምንረዳበት ሁኔታ ይኖራል።

ብዙ ጊዜ የአንድን መሪ ችሎታና ለሥራው ማደግ ያደረገውን አስተዋጽዖ በትክክል የምንረዳው እርሱን ስናጣው ነው። የሙሴን ታላቅ መሪነት እስራኤል ያወቁት እርሱ ከሞተ በኋላ ነበር። የአንድ ታላቅ ሰውን ሞት ስናስብ፣ በሕይወቱ ያስተማራቸውን ትምህርቶች ከበፊቱ የበለጠ ከበፊታ እንሰጣቸዋለን።

በሌላ በኩል ደግሞ፤ የአንድ መሪ ከቦታው መነሣት ከእግዚአብሔር ሥራ ስፋት አንጻር ስንመለከተው የሰውየውን ውስንነት ያሳየናል። ሰውየው ይሞታል፤ ሥራው ግን አይሞትም። የቱንም ያህል ታላላቅ ሥራዎችን ያከናወነ ቢሆንም፤ መተኪያ አይገኝለትም ማለት አይደለም። የእርሱ እገዛና አስተዋጽኦ የማያስፈልግበት ወይም የሚያበቃበት ጊዜ ይመጣል። ማንኛውም የተሰየ ስጦታ አለው የሚባል አገልጋይ የራሱ ውስንነት አለው፤ ይህም ግልጽ የሚሆነው

እርሱን የሚተካው ሰው ሥራውን በተሻለ ሁኔታ ሠርቶ ሲገኝ ነው። የበፊቱ መሪ መሥራት ያልቻለውን ሁለተኛው መሪ ሊሠራው ይችላል። አንዳንድ ጊዜ የተለያዩ ስጦታዎች ያሉት ታናሽ የምንለው ሰው ሥራውን ከጀመሩትና ከእርሱ በፊት ከነበሩ ሰዎች ይልቅ ከፍተኛ ነገሮችን ሲያከናውን ይገኛል። ምናልባትም ሙሴ የከነዓንን ምድር ለእስራኤል ልጆች የማከፋፈሉ ሥራ የኢያሱን ያህል ላይዋጣለት ይችል ይሆናል።

ብርቱና ጠንካራ መሪ ከቦታው ሲነሣ፣ የተሻለ ብቃት ያለው ሌላ መሪ መነሣት በር ሊከፈት ይችላል። አንዳንድ ጊዜ የበታች ሆነው ሲሠሩ የነበሩ ሰዎች ከባድ ኃላፊነት ሲጣልባቸው ይኖራቸዋል ተብሎ ባልታሰበ ችሎታ ሥራውን ሲያቀላጥፉ ይታያል። የተጣለባቸው ኃላፊነት ጫና በውስጣቸው የታመቀውን ችሎታና ብቃት ያወጣዋል። ሙሴን በማገልገል ብቻ ተወስኖ ቢቀር ኖሮ ምናልባት የኢያሱን መሪነት ችሎታ ማየት ባልተቻለ ነበር።

አንዱን አገልጋይ በሌላው የመተካቱ ሂደት የሚፈለገው ግብ ላይ እስኪደርስ ድረስ እግዚአብሔር በተለያዩ ሰዎች መጠቀም እንደሚችልና ሥራው በአንድ ሰው ተጀምሮ በዚያው ሰው የሚጠናቀቅ ሳይሆን በቅብብሎሽ የሚሠራ እንደሆነ እናያለን። እርሱ ያስጀመረውን ሥራ የማስጨረስ አቅሙ በፍጹም አይሚጠጥም። ታላላቅ ስጦታዎች ያሉት ሰው ስጦታዎቹን ለእግዚአብሔር ሥራ ባያውል እንኳ እግዚአብሔር በዚህም አይሸነፍም። ሙሉ በሙሉ ራሱን የሰጠ፤ ከእርሱ ያነሰ ስጦታ ያለውን ሰው ያስነሣና የራሱን ኃይልና ብርታት ሰጥቶ ሥራውን ያሠራዋል። አስተዋይና ተመራማሪ ለነበሩ የቆሮንቶስ ሰዎች ጳውሎስ በጻፈው መልእክት ይህንኑ እውነት ነው የነገራቸው፦ «ወንድሞች ሆይ፣ በተጠራችሁ ጊዜ ምን እንደነበራችሁ እስቲ አስቡ፤ በሰው መስፈርት ከእናንተ ብዙዎቻችሁ ዐዋቂዎች አልነበራችሁም፤ ብዙዎቻችሁም ኃያላን አልነበራችሁም፤ ብዙዎቻችሁም ከትልቅ ቤተ ሰብ አልተወለዳችሁም። ነገር ግን እግዚአብሔር ጥበበኞችን ያሳፍር ዘንድ የዓለምን ሞኝ ነገር መረጠ፤ እግዚአብሔር ብርቱዎችን ያሳፍር ዘንድ የዓለምን ደካማ ነገር መረጠ። እግዚአብሔር የተከበረውን እንደሌለ ለማድረግ በዚህ ዓለም ዝቅ ያለውንና የተናቀውን ነገር፤ ቦታም ያልተሰጥውን ነገር መረጠ፤ ይኸውም ማንም ሰው በእርሰ ፊት እንዳይመካ ነው። (1ኛ ቆሮ. 1:26-29 አ.መ.ት)።

ችግሩ፣ ሰዎች ባላቸው ትንሽ ኃይልና ስጦታ እግዚአብሔር መጠቀም አለመፈለጉ አይደለም፤ ችግሩ እንደ ጳውሎስ ሁሉ ያላቸውን ኃይልና ስጦታ ለእግዚአብሔር ሥራ ሙሉ በሙሉ ለመስጠት ፈቃደኛ

አለመሆናቸው ነው። እንዲህ ያሉ ሰዎች በራሳቸው ኃይልና ጥበብ መደገፍን ትተው በእግዚአብሔር መደገፍን ሲጀምሩ ወሰን ወይም ገደብ በሌለው ሁኔታ ለራሱ ክብር ይጠቀምባቸዋል።

የአንድ ታላቅ ሚሲዮናዊ ተቋም መሥራች የነበሩ ኤ.ቢ. ሲምፕሰን የሚባሉ ሰው ለመሞት ተቃርበው በነበረ ጊዜ በተደረገ ስብሰባ የአንድ ቤተ ክርስቲያን መሪ ይነሣና የእርሳቸውን ያህል ችሎታ ያለው ሰው ማግኘት ስለማይቻል እርሳቸው ከሞቱ በኋላ ሥራው እንዲቀጥል ከተፈለገ በጣም ብዙ ገንዘብ መሰብሰብ እንደሚገባ ይናገራል። እርሳቸው ግን ምንም አልተናገሩም፤ ምንም አላደረጉም። ምክንያቱም፣ ሥራው የእግዚአብሔር ከሆነ ምንም ሊያፈርሰው የሚችል ኃይል እንደማይኖር ስለሚያውቁ ነበር፤ ከእግዚአብሔር ካልሆነ ደግሞ በበጐ ዓላማ የተነሣሡ ሰዎች ድጋፍ እንዲቀጥል እንደማያደርገው ስለ ተገነዘቡ ነበር።

ከመሞታቸው ጥቂት ቀደም ብሎ ከኃላፊነት ቦታቸው ተነሥተው በነበረ ጊዜ ሰዎች ብዛት ያለው ገንዘብ ለሚሲዮናዊ ዓላማ እየሰጡ እንደሆነ፣ በውጭ አገሮች የሚደረገው የሥራ እንቅስቃሴም እየሰፋና እየተደራጀ እንደሆነ በሚደርሳቸው ሪፖርት በጣም ደስተኛ ነበሩ። እንዲያውም ያ ድርጅት በታሪኩ ታይቶ የማይታወቅ እድገትን ያስመዘገበው እርሳቸው ከሞቱ በኋላ ነበር። ለታላቅ መሪነታቸው ከዚህ የበለጠ ዋጋ ሊከፈላቸው አይችልም።

መተኪያ የሌለው አንድ መሪ ብቻ አለ፤ አሁንም ሆነ ለዘላለም በሥልጣኑ ላይ ስለሆነ ምትክ አያስፈልገውም። ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ ደቀ መዛሙርቱ እርሱን የሚተካ ሰው ለመምረጥ ዝግጅት ሲያደርጉ አንመለከትም፤ ይህም የሚያሳየው የምን ጊዜም መሪያቸው መሆኑን መቀበላቸውን ነው። እርሱ ሞት ሆነ እርጅና የማይሸረው ሕያው መሪያቸው ነው። አንዳንድ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን የእርሱ መገኘት ኃይል ግልጽ በሆነ ሁኔታ ላይታወቃት ይችላል፤ ያም ሆኖ ግን ያለ መሪ የነበረችበት ጊዜ አልነበረም። የቤተ ክርስቲያኑ ሀዘንና ጭንቀት፣ የእርሱ ሀዘንና ጭንቀት መሆኑን ክርስቶስ በተለያየ ሁኔታ አሳይቶአል። «ቤተ ክርስቲያን የእርሱ ከሆነች፣ እርስዋን መጠበቅ፣ መከላከልና ደግፎ ማቆም የእርሱ እንጂ የእኛ ሥራ አይደለም። እኛ ያን ማድረግ ብንችል ኖሮ ከሰማይ በታች የእኛን ያህል ኩሩና ትዕቢተኛ ትውልድ ሊኖር አይችልም ነበር» ይላል ማርቲን ሉተር ጌታ የቤተ ክርስቲያን አጋዥና ጠበቃ መሆኑን ሲናገር። በዘላለማዊ ኃይሉ ሥራውን መፈጸም የሚችል መሪ አለን፤ ዛሬም፣ ነገም ለዘላለምም ቢሆን የመሪዎች መለዋወጥ ሊያስደንቀንና ሊያናውጠን አይችልም።

20
ተተኪ አገልጋዮችን ስለ ማፍራት፤ ስለ ማሠልጠን

«ብዙ ሰዎች የመሰከሩለትን፣ ከእኔም የሰማኸውን ሌሎችን ደግሞ ሊያስተምሩ ለሚችሉ ለታመኑ ሰዎች አደራ ስጥ»

(2ኛ ጢሞቴዎስ 2:2)

ከላይ በተመለከትነው ጥቅስ ጳውሎስ አንድ መንፈሳዊ መሪ ተተኪዎችን ማፍራትና እርሱን መሰል አገልጋዮችን ማሠልጠን እንዳለበት ይናገራል። ለዚሁ ጉዳይ ጊዜውንና ሁለንተናውን ከሰጠ እርሱን የሚመስሉ፣ ምናልባትም ከእርሱ የሚበልጡ ወጣት አገልጋዮችን ማሠልጠን ይችላል። ጳውሎስና በርናባስ በአንድነት እያገለገሉ ነበር፤ በጊዜ ሂደት ግን ጳውሎስ የአገልግሎት ቡድኑ መሪ ሆኖ በመገኘቱ በርናባስ ቅንዓት ወይም ምቀኝነት አላደረበትም፤ በዚህም መንፈሳዊ ትልቅነቱን አሳይቶአል። አብረውት ወይም ከእርሱ በታች ሆነው የሚሠሩ ሰዎች የአመራር ችሎታቸውን እንዲያሻሽሉ አንድ መሪ የሚቻለውን ሁሉ ማደረግ ይጠበቅበታል። መሪዎች የሚተካቸውን ሰው ማሠልጠንና ችሎታውንም የሚያስመሰክርበት ዕድልና አጋጣሚውን ማመቻቸት ይኖርባቸዋል፤ ይህንንም ማድረግ የሚቻለው ኃላፊነት መሸከምን እንዲለማመዱና በራሳቸው ዕቅድ እያወጡ ተግባር ላይ የሚያውሉበትን ምቹ ሁኔታ በማዘጋጀት ነው። ስለሚያደርጉት አስተዋጽኦም ተገቢውን ማበረታቻና ድጋፍ መስጠትን መዘንጋት የለበትም። ከሁሉ ይልቅ ትልቁ ጉዳይ የተሰጣቸውን ሥራ በሚገባ መወጣት እንደሚችሉ እምነት ሊጣልባቸው ይገባል። የሚሠራ ሰው መሳሳቱ ያለ ነገር በመሆኑም መሪዎችን ስናሠለጥን መሳሳትና ከስሕተት መማር እንደ አዲስ ነገር መታየት የለበትም።

በቅርቡ ተደርጐ በነበረ አንድ የሚሲዮናውያን ኮንፈረንስ ላይ ከአንድ ሚስዮናዊ የሚጠብቀው ምን እንደሆነ ለአገሬው ሰዎች ጥያቄ ቀርቦላቸው ነበር። የአገሬው አገልጋይ ሲናገር፦ «ሚሲዮናውያን፣ ሌሎችን ማለትም ተተኪ የአገሬው አገልጋዮችን ማሠልጠን እንጂ ሁሉንም ነገር እነርሱ ብቻ መሥራት የለባቸውም» ነበር ያለው። የሚፈለገውም ይኸው ነው።

የወደፊት መሪዎችን ማሠልጠን ቀላል ጉዳይ ባለመሆኑ ተገቢ ጥንቃቄ ያሻዋል። አስተዋይ መሪ ተተኪዎችን ያሠለጥናል እንጂ የማሠለጥናችሁ መሪዎች እንድትሆኑ ነው በማለት ቀድሞ አይናገርም። ስቲፈን ኔል የተባሉ አንድ ጳጳስ የዚህ ዓይነቱ አቀራረብ ሊያስከትል ስለሚችለው አደጋ የረጅም ጊዜ ልምዳቸውን መሠረት በማድረግ ሲናገሩ፦ «ሰዎችን ሁሉ ለመሪነት ለማሠልጠን የምናደርገው ሙከራ ውጤቱ እረፍት የሌላቸው፣ በምኞት የተሞሉና በአእምሮ እውቀታቸው ብቻ የሚደገፉ መሪዎችን ማፍራት ይሆናል። አንድን ሰው መሪ እንድትሆን ተጠርተሃል ማለት ከማንኛውም ነገር ይልቅ ያንን ሰው ለመንፈሳዊ ውድቀት ማጋለጥ ከመሆኑም በላይ አገልግሎቱን ፍሬ ቢስ ያደርገዋል። ትልቁ ጉዳይ የወደፊት አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች መንፈሳዊና የኃላፊነት ቀንበርንም ለመሸከም ብቁ የሆኑ ሰዎችን እንጂ ቶሎእምሮ እውቀታቸው የሚመኩ፣ በከፍተኛ ምኞት የተነሣሡ ሰዎችን ማፍራት አይደለም» ብለዋል።

በመሠረቱ፣ ስለ መሪነት ያለን ጽንሰ አሳብ ምንድን ነው? ማፍራት የምንፈልገውስ ምን ዓይነት መሪዎችን ነው የሚለው ራሱ አጠያያቂ ነው። አንዳንድ ጊዜ ስለ መሪነት ስናስብ የምንከተለው መርሐ ከዓለማውያን አሠራር ጋር እየተጋጨ ችግር ይፈጥርብናል። በመሠረቱ፣ ዋናው ትኩረታችን እውነተኛ ቅዱሳንን፣ ለአገልግሎት ራሳቸውን የሚሰጡ መንፈሳውያን ሰዎችን ማፍራት እንጂ አለቃ ማፍራት ላይ መሆን የለበትም፤ ለመሪነት ስንል ብቻ ሰዎችን የምናዘጋጅ ከሆነ ውድቀቱ አስከፊ ይሆናል። ክርስቲያን መሪዎችን ስናሠለጥን ምሳሌያችን ጌታ አሠራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት ሲያዘጋጅ የተጠቀመበት መንገድ መሆን አለበት።

በአሁኑ ዘመን ፍሬያማ ሆኖ የተገኘው አሠራር የወደፊት ቤተ ክርስቲያን መሪዎች እምቅ ክህሎታቸውን አውጥተው ሥራ ላይ እንዲያውሉት ማገዝና ማበረታታት ነው። ይህም ከፍተኛ ጥንቃቄን፣ በማስተዋል እቅድ ማውጣትን፣ ከፍተኛ ትዕግሥትንና እውነተኛ ክርስቲያናዊ ፍቅርን ይጠይቃል፤ ባወጣ ያውጣው ብለን የምናደርገው ጉዳይ አይደለም። ጌታችን በሦስት ዓመት አገልግሎቱ አብዛኛውን ጊዜ ያጠፋው ደቀ መዛሙርቱን በማስተማር፣ በማሠልጠንና፣ ጸባያቸውን በማበጀትና በማስተካከል ነበር። ይህን ማድረግ ሰፊ ጊዜ ቢጠይቅ እንኳ፣ ከሚፈለገው ዓላማ አንጻር ይህ ለእርሱ ምንም አልነበረም። ተስፋ የሚጣልባቸው የወደፊት መሪዎችን ማለት ጢሞቴዎስና ቲቶን ለማሠልጠን ጳውሎስ ጌታ በተጠቀመበት መንገድ ነበር የተጠቀመው።

የኋላ ኋላ ጢሞቴዎስ የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያንን በመምራት ሲያገለግል ነበር፤ እርሱን ለዚያ ደረጃ ለማብቃት ጳውሎስ የተጠቀመበት ዘዴ በዚህ ዘመን ላለነውም ምሳሌ ሊሆነን የሚችል ነው። ጢሞቴዎስ ለአገልግሎት ሲዘጋጅ የሃያ ዓመት ወጣት ሳይሆን እንዳልቀረ ይታሰባል፤ ያደገው በአናቱና በሴት አያቱ እንደመሆኑ መጠን የመለሳለስ ባሕርይ እንዲኖረው ተጽዕኖ ሳያደርግበት አልቀረም። በዚህ ላይ ደግሞ ታማሚ ስለነበር የሚፈለገውን ያህል ታታሪ ሠራተኛ ላይሆን ይችላል። ዓይናፋርና ቅልስልስነቱንም ጳውሎስ በየጊዜው ማረምና ማስተካከል ነበረበት። በነገር ሁሉ ብርቱና ጠንካራ ሆኖ መገኘት እንዳለበት ከተጻፈለት መልእክት መመልከት ይቻላል። ትልልቅ መስለው ለሚታዩት ሰዎች ከሚገባ በላይ ትኩረት ይሰጥ ነበር፤ በሚነሳበት ተቃውሞም በቀላሉ ይደናገጥ ነበር። የተዳፈነ መንፈሳዊ ስጦታውን በማቀጣጠል ወደፊት ከመሄድ ይልቅ፣ ባለፈ ዘመን ልምምዱ ብቻ የመወሰን ዝንባሌ ነበረው። ጳውሎስ ግን ለጢሞቴዎስ ላቅ ያለ ደረጃን ነበር የሚያስብለት፤ መከራና ችግር እንዲያናውጠው አይፈልግም። ከአቅሙ በላይ ኃላፊነትን እየሰጠ ወደፊት ለሚጠብቀው ከፍተኛ የመሪነት ሥራ ያለማምደው ነበር። ታዲያ፣ አንድ ወጣት ከባድ መስለው የሚታዩ ችግሮችን መጋፈጥ ካልተለማመደና ወደፊት ለሚጠብቀው ኃላፊነት ካልተዘጋጀ በሌላ አቋራጭ እንዴት አቅሙን ማጐልበት ይችላል?

ከጳውሎስ ጋር መጓዙ ከተለያዩ ሰዎች ጋር እንዲገናኝ ለጢሞቴዎስ ምቹ ሁኔታን ፈጥሮለታል፤ ምኞትና ፍላጐቱን ጤናማ በሆነ መልኩ ማነሣሣት ከሚችሉ ታዋቂ ሰዎች ጋር ለመተዋወቅ ችሎአል። በሕይወትና በአገልግሎቱ ጳውሎስን የተለያዩ ችግሮች ይገጥሙት ነበር፤ ስለዚህ ለችግሮች እጅ አለ መስጠትንና በአሸናፊነት መወጣትን ጢሞቴዎስ የተማረው ከዚሁ የቅርብ መምህሩ ነበር። የጳውሎስን የስብከት ሥራ ይካፈል ነበር። በተሰሎንቄ የነበሩ ክርስቲያኖችን የማበረታታትና በእምነታቸው የማሳደግ ኃላፊነትም ተሰጥቶት ነበር፤ የተጣለበትንም አደራ በአግባቡ ተወጥቶአል። ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ላቅ ያለ ግብ አስቀምጦለታል፤ ትልልቅ ነገሮችንም ይጠብቅበት ነበር፤ ይህንንም በማድረጉ በጢሞቴዎስ ውስጥ የነበረው እምቅ ችሎታና ኃይል እንዲወጣ አድርጐአል። ምናልባትም ተራ ከመሆን ደረጃ አውጥቶ ጢሞቴዎስን ከታላላቆች ጐራ ለመመደብ ያስቻለው ይኸው ሳይሆን እንዳልቀረ አስባለሁ።

ሁኔታዎችን በንቃት የሚከታተል መሪ ለምንም ይጠቅማሉ ተብለው ከማይገመቱ ሰዎች ውስጥ እንኳ እምቅ የመሪነት ችሎታና

አቅም መኖሩን ይረዳል። አንድ መሪ ከእርሱ የተሻሉ ተተኪ መሪዎችን ማሠልጠን ካልቻለ የጀመረው ሥራ ቀጣይነት አይኖረውም።

በሚስዮናዊነት ሥራ ከፍተኛ ስፍራ የሚሰጠው ጉዳይ ቢኖር ከአገሬው ሰዎች መካከል መንፈሳዊነት ያላቸውን ሰዎች ለመሪነት ማሠልጠን ነው፤ ምክንያቱም የወደፊት አብያተ ክርስቲያናት እድገት የሚወሰነው በእነርሱ በመሆኑ ነው። ዋነኛው ተልዕኮ ከተከናወነ በኋላ ቀጣዩ ነገር ተተኪ ወይም መሰል ሰዎችን የማሠልጠኑ ሥራ ነው። ወጣት የወንጌል አገልጋዮችም እንዲሁ በተራቸው መሰል አገልጋዮችን ከማፍራት መታቀብ የለባቸውም።

ወጣት አገልጋዮችን ስናሠለጥን አንዳንድ ለየት ያሉ አጋጣሚዎ ሊኖሩ ስለሚችሉ ሁልጊዜ አንድ ዓይነት አሠራርን ብቻ መከተል ላያስፈልግ ይችላል። እግዚአብሔር ባልተለመዱ ሁኔታዎች የራሱን ሰው ማስነሣት ይችላል፤ በዚህ መልክ እርሱ የሚያስነሣቸውም ወንጌልን በዓለም በማዳረሱ ረገድ ያልተጠበቀ ውጤት ማስመዝገባቸው ይታወቃል። ስለዚህም ለእንዲህ ዓይነት አጋጣሚዎች ስፍራ መስጠት ይኖርብናል። እንዲህ ያሉ አገልጋዮች እግዚአብሔር በራሱ ጊዜ የሚያስነሣቸው ስለሆኑ በሰው መለኪያና መስፈርት የሚመዘኑ አይደሉም። እንዲያማ ባይሆን ኖሮ አንዳንድ አገልጋዮችን ማን ለዚህ ይበቃሉ ብሎ ይጠብቅ ነበር? ይሁን እንጂ እንዲህ ያሉ ሰዎች በአገልግሎት ከፍተኛ ውጤት ሲያስመዘግቡ ታይቶአል።

እንዲህ ካሉ አገልጋዮ አንዱ ዳግላስ ቶርንተን ናቸው፤ እኚህ ሰው እስላሞችን በወንጌል ለመድረስ በተደረገ እንቅስቃሴ ዐቢይ ውጤት ማስመዝገባቸው ይታወቃል። በብዙዎች ዘንድ በቀላሉ የማይገኙ ስጦታዎች ነበሩዋቸው፤ ላገለገሉበት የሥራ መስክ እጩ ሆነው በቀረቡ ጊዜ ለበላዮቻቸው የሚያቀርቡት አሳብ ሥር ነቀልና በተግባር መተርጉም የማይቻል እንደሆነ ታስቦ ነበር። ይህን በተመለከተ የሕይወት ታሪካቸውን ያዘጋጀ ሰው እንዲህ በማለት አስፍሮአል፦

> «በግብፅ አገር እያከናወኑ ስለነበረው ሥራ የወደፊት እቅድ አስመልክተው የጻፉት በጣም የሚገርም ነው። በሚስዮናዊ ሥራ መስክ ያን ያህል አጭር ጊዜ ካገለገሉ ወጣቶች ይህ በፍጹም የሚጠበቅ አልነበረም። ሚስዮናዊ ባለሥልጣናቱም ያንን እቅድ ተመልክተው በፍጹም የማይቻል ነው በማለት አስበው ነበር። ይሁን እንጂ፣ እርሳቸው የተለዩ ሰው ነበሩ፤ ውሎ አድሮም የሥራ እቅዳቸው የባለሥልጣናቱን ትኩረት አግኝቶአል።»

መንፈሳዊ መሪ

የወደፊት መሪዎችን ማሠልጠንን በተመለከተ ዋናው ትኩረታችን ሰዎችን በብዛት ማሠልጠን የምንችልበት ዘዴ ላይ መሆን እንደሌለበት መናገር አስፈላጊ ነው። በትዕግሥትና በጥንቃቄ እንዲሁም በጸሎት መንፈስ ሰዎችን በቅርብ ሆነን መከታተል ይኖርብናል፤ ይህም ራሱ ረጅም ጊዜ ሊወስድ ይችላል። «እንደ ፋብሪካ ዕቃ ሁሉ ደቀ መዛሙርትን በገፍ ማምረት አይቻልም። ደቀ መዛሙርትን ማፍራት የሚቻለው አንድ በአንድ ወይም በጥቂት በጥቂቱ ነው፤ ወጣቶቹን ለወደፊት መሪነት ለማሠልጠን በቅርብ ሆኖ ማስተማር፣ መመሪያ መስጠት፣ መኰትኰትና ማሳደግ ያስፈልጋል።»

አንድ ሰው በእርግጥ በእግዚአብሔር ለመሪነት የተመረጠ ከሆነ፣ ለሥራው ብቁ ለመሆን የሚስፈልገውን ማንኛውንም ሁኔታ እርሱ ራሱ ያመቻችለታል።

እግዚአብሔር አንድን ሰው መቅረጽ፣ መሥራትና ማበጀት ከፈለገ ዓለም ሁሉ የሚደነቅበት አድርጐ ያቆመዋል፤ የተለያዩ ችግሮችና ፈተናዎች ቢጋረጡበት እንኳ ያንን ሰው እንዴት በዚያ ውስጥ እንደሚሳልፈው ያውቃል።

21

መንፈሳዊውን መሪ ሊገጥሙት የሚችሉ አንዳንድ ፈተናዎች

ነገር ግን ለሌሎች ከሰበክሁ በኋላ ራሴ የተጣልሁ እንዳልሆን ሥጋዬን እየገሰምሁ አስገዛዋለሁ

1ኛ ቆሮንቶስ 9:27::

በየትኛውም የሥራ መስክ የተሰማሩ ሁሉ የተለያዩ ፈተናዎች እንደሚገጥሙዋቸው ቢታወቅም መንፈሳዊውን መሪ የሚገጥሙት ፈተናዎች ግን በዓይነታቸው የረቀቁና ከፍተኛ ጥፋትን የሚያስከትሉ ናቸው:: እንደማንኛውም ሰው ሁሉ መሪውም ለተለያዩ የሥጋ ፈተናዎች ይጋለጣል፤ ይሁን እንጂ በጣም አደገኞቹ ከመንፈሳዊ ሕይወት አኳያ የሚመጡት ናቸው:: ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ያለበትም ይህን በተመለከተ ነው:: ባላጋራው ሰይጣን በማንኛውም የሕይወት ገጽታው እርሱን ለመጣል ሌት ተቀን በትጋት እንደሚሠራ መሪው መገንዘብ ይኖርበታል:: አገልጋዩን የሚገጥሙት ፈተናዎች በጣም ብዙ ቢሆኑም የሚከተሉት ጥቂቶቹ ግንባር ቀደሙን ስፍራ ይይዛሉ::

በትዕቢት ሊፈተን ይችላል

ከሌሎች ይልቅ ለኃላፊነት መመረጡ፤ በግልጽም ባይሆን እንኳ በስውር አገልጋዩ ትዕቢት እንዲያድርበት ምክንያት ሊሆነው ይችላል፤ ይህም በጊዜው እርማት ካልተደረገበት ለእግዚአብሔር መንግሥት መስፋፋት ስንኩል ያደርገዋል፤ ምክንያቱም:- «በልቡ የታበየ በእግዚአብሔር ዘንድ እርኩስ ነውና» (ምሳ. 16:5):: ምንኛ ብርቱ ቃል ነው! ምንኛ ራሳችንን እንድንመረምር የሚያደርግ ቃል ነው! የትዕቢትን ያህል እግዚአብሔር የሚጠላውና የሚጸየፈው ኃጢአት የለም ማለት ይቻላል:: በመሠረታዊ ባሕርዩ ስንመለከተው ትዕቢት ከእግዚአብሔር ይልቅ ራስን ማዋደድና ከፍ ከፍ ማድረግ ነው:: ከክብር ስፍራው ሰይጣንን የጣለ ትዕቢት ነበር፤ ከዚያ በፊት ግን ሰይጣን የተቀባ ኪሩብ ነበር፤ በእግዚአብሔር ዙፋን ዙሪያ ከሚቆሙ ከታላላቆቹ መላእክትም አንዱ ነበር::

ትዕቢት በተለያየ መልክና አሠራር ሊገለጥ ይችላል፤ ከሁሉም ይልቅ አስከፊው ግን መንፈሳዊ ትዕቢት ነው:: እግዚአብሔር በሰጠን መንፈሳዊ ስጦታዎች መታበይ፤ ከፍቅርና ከጸጋው የተነሣ እርሱ

ባስቀመጠን ከፍተኛ ስፍራ መመካት፣ መጀመሪያውኑ ጸጋ የእግዚአብሔር ስጦታ እንጂ የእኛ አለመሆኑን አለማወቃችንን ነው የሚያሳየው፤ አለን የምንለው ነገር በሙሉ ከእርሱ የተቀበልነው እንጂ የራሳችን አይደለም።

በጣም የሚገርመው ደግሞ ሰዎች መታበይ ሲጀምሩ ላይታወቃቸው መቻሉ ነው። ስለሆነም ትዕቢት እያጠቃን መሆን አለመሆኑን ራሳችንን የምንመዝንባቸው ሦስት መስፈርቶች ቀርበዋል።

ኬሎች ይልቅ ጐላ ብሎ የመታየት አዝማሚያ። ለራሳችን በምንመኘው ስፍራ ወይም በምንጓጓለት ደረጃ ሌላው ቢመረጥ ምን ይሰማናል? እኛ ተረስተን ሌላው ዕድገት ሲያገኝስ እንዴት እንቀበለዋለን? ባለው ስጦታና ባከናወነው ተግባር ከእኛ ይልቅ ሌላው ደምቆ ቢታይ ምንድን ነው የሚሰማን?

ምን ያህል ቅኖችና እውነተኞች ነን? ብዙ ጊዜ ብቻችንን ሆነን ራሳችንን ስንመረምር እኛነታችንን በተመለከተ ብዙ የምንለው ይኖረናል። ግን፣ እነዚያኑ ስለ ራሳችን የምንቀበላቸውን ነገሮች ሌላው በተለይም እንደ ተፎካካሪ የምንቆጥረው ሰው ቢናገር ምንድን ነው የሚሰማን? ደንሞች ነን እንላለን፤ ደካማነታችንን ሌላው ሲናገር እንዴት ነው የምንቀበለው?

ነቀፋና ትችትን የምናስተናግድበት ሁኔታ። ነቀፋና ትችት የሚሰነዝሩብን ሰዎች እንጠላለን? ቅርታና ምሬትስ ያድርብናል? ስንነቀፍ ስለ ራሳችን መልስ ለመስጠት በቁጣ ቱግ ብለን እንነሣለን? ነቃፊውን መልሰን እንነቅፋለን?

ቅንና እውነተኛ ሆነን በመስቀል ላይ ለመሞት ራሱን ትሑት ካደረገው ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት ጋር ሕይወታችንን ስናስተያየው ምን ያህል ዓመፀኛና ጸያፍ እንደሆነ እናያለን። ትዕቢታችንን በእውነተኛ መልክና ገጽታው ብናየው ኖሮ፦ «ትዕቢት ጥፋ፤ ትምክህትም ዘወር በልልኝ፤ ስለ ራሴ የማውቀው በጸጋ የዳንሁ ኃጢአተኛ መሆኔን ብቻ ነው» የሚል ዋይታ ባሰማን ነበር።

በራስ ወዳድነት ሊፈተን ይችላል

ራስ ወዳድነት ትዕቢት ራሱን ከሚገልጽበት አስቀያሚ ገጽታዎች አንዱና ዋነኛው ነው። ራስ ወዳድ ሰው ስለ ራሱ የተጋነነ አመለካከት አለው፤ ስለ ራሱ ብዙ ያወራል፤ ስላከናወነው ተግባር ወይም ስለ አስፈላጊነቱ ከመጠን በላይ የተጋነነ አስተሳሰብ ተጠናውቶል። ነገሮችን የሚመዝነው ከራሱ አኳያ እንጂ ለእግዚአብሔር በሚያስገኘው ክብር ወይም ለሌሎች ከሚሰጠው ጥቅም አንፃር አይደለም። በሌሎች ብዙ

የሚደነቅና የተለየ ተደርጐ የሚታይ መሪ ከማንም ይልቅ ለዚህ ውድቀት ይጋለጣል።

ሮበርት ስቲቬንሰን የሚባሉ አገልጋይ ሳምዋ የሚባል አገርን በጐበኙ ጊዜ በአንድ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ለሚማሩ መጋቢያንና ሌሎች ተማሪዎች ንግግር እንዲያደርጉ ይጋበዛሉ። በንግግራቸው መሐል ስለ አንድ ነቢይ ነኝ ስለሚልና ሁልጊዜ ፊቱን ሸፍኖ ስለሚታይ ሰው የተናገሩትን እዚህ ላይ ማንሳት አግባብነት ይኖረዋል። ሰውየው በዘመኑ ከነበሩ መምህራን ሁሉ ደምቆ የሚታይና በእውቀቱም የተደነቀ ነበር። ታዲያ፣ አንድ ቀን ለምን ሁል ጊዜ ፊቱን እንደሚሸፍን ለቀረበለት ጥያቄ ሲመልስ «እንደዚያማ ባላደርግ ኖሮ እኔ ላይ ካለው ክብር የተነሣ ማንም በፊቴ መቆም አይችልም ነበር» ይላል።

ጊዜ ጊዜን እየተካ በሄደ መጠን ያቺ ፊቱን የሚሸፍንባት መጐናጸፊያ እያረጀችና እየተቀዳደደች ትሄዳለች። ሰዎቹም መጐናጸፊያዋ አስቀያሚ ፊቱን የሚሸፍንባት እንጂ ሌላ ምንም እንዳልሆነች ይረዳሉ። ይህንን መሠረት በማድረግ ስቲቬንሰን ሲናገሩ «አንድ ሰባኪ የቱንም አስደናቂ እውነትን መግለጥ ቢችልም፣ ብልሹ ባሕርዩንም በረቀቀ ጥበብና አቀራረብ ማድበስበስ ቢያውቅበትም፣ አንድ ቀን ሽፋኑ ሲወድቅ ሰዎች እውነተኛ ማንነቱን ማወቃቸው አይቀርም። ስለዚህም ምን ጊዜም ትዕቢተኛ አትሁኑ። ይልቁንም ትሕትናን፣ ቅንነትና እውነትን መከታተል ይኖርባችኋል» አሉ። መጋረጃው ሲነሣ አስቀያሚ የራስ ወዳድነታችን ገጽታ ወይም ክርስቶስን መሰል ባሕርያችን ለሰዎች ሁሉ ይገለጣል።

> «በውስጣችን ራስ ወዳድነት መኖር አለመኖሩን ስለሚያሳውቀን አንዳንዴ ከሰዎች የምንሰማው ምስጋናና ሙገሣ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። ይሁን እንጂ ሌላው ሰው፣ በተለይም ተፎካካሪያችን ሲመሰገንና ሲሞገስ ያለምንም ቁጣና ጣልቃ ገብነት መስማት ካልቻልን አደገኛ የራስ ወዳድነት በሽታ ተጠናውቶናል ማለት ነው፤ ስለሆነም ይህን ኃጢአት ቶሎ ልንናዘዘውና ልናስወግደው ይገባል።»

አገልጋይ በቅንዓትና በምቀኝነት ሊፈተን ይችላል

ቅንዓትና ምቀኝነት ከትዕቢት ጋር የጠበቀ ግንኙነት አላቸው። ምቀኝነትና ቅንዓት የሚያጠቁት ሰው ሌሎችን በተለይም ደግሞ የሚያሰጉ ናቸው የሚላቸውን ሁሉ በጥርጣሬ ይመለከታል። ሙሴ በጣም ይወደውና ያቀርበው የነበረ ኢያሱ ይመጣና፦ «ኤልዳድን

ሜዳድ በሰፈር ውስጥ ትንቢት እየተናገሩ ነውና እባክህን ከልክላቸው» ይለዋል (ዘኁ. 11:28)። እንዲረዱትና እንዲያግዙት እነዚህን ሁለት ሰዎች የመረጣቸው ሙሴ ራሱ ነበር፤ አሁን ደግሞ የእግዚአብሔር መንፈስ ስለነካቸው ትንቢት እየተናገሩ ነበር። ይህን የተመለከቱ ሌሎች ደግሞ ለሙሴ ነቢይነት በመቆርቆር በቅንዓትና በምቀኝነት ተነሣሥተዋል። ከእግዚአብሔር ጋር ፊት ለፊት መነጋገርን በተለማመደው ሙሴ ውስጥ ግን ቅንዓትና ምቀኝነት ምንም ስፍራ አልነበራቸውም። ነገሮችን እርሱን ለጠራው አምላክ መተው እንዳለበት በሚገባ ተገንዝቦ ስለነበር «የእግዚአብሔር ሕዝብ ሁሉ ነቢያት ቢሆኑ. . . አንተ ስለ እኔ ትቀናለህን?» በማለት አሳፍሮታል። ለእግዚአብሔር ክብር የሚቈረቆር መሪ ለራሱ ክብርና ዝና አይቈረቈርም። እንዲህ ያሉ ነገሮችንን ለእግዚአብሔር ይተዋል።

ዝነኛ ወይም ታዋቂ በመሆን ስሜት ሊፈተን ይችላል

ትልቅነትን ወይም ታዋቂና ዝነኛ ሆኖ ለመገኘት የሚደረግ ሙከራ የፖለቲካ ቡድን መሪዎችን ብቻ የሚያጠቃ አይደለም። ይህ ዓይነቱ ዝንባሌ በጳውሎስ ዘመን ነበር፤ ዛሬም ከእኛ ጋር አለ። አንዳንድ ማስተዋል የጐደላቸው ሰዎች ለመንፈሳዊ መሪዎቻቸው የተጋነነ አመለካከት አላቸው፤ አንዱን ከፍ ሌላውን ዝቅ የማድረግ ዝንባሌም ይታይባቸዋል።

ይህ አዝማሚያ በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን በስፋት ይታይ ነበር፤ «አንዱ እኔ የጳውሎስ ነኝ ሁለተኛውም እኔ የአጵሎስ ነኝ ቢል ሰዎች ብቻ መሆናችሁ አይደለምን? አጵሎስ እንግዲህ ምንድን ነው? ጳውሎስስ ምንድን ነው? በእነርሱ እጅ ያመናችሁ አገልጋዮች ናቸው። ለእያንዳንዳቸውም ጌታ እንደሰጣቸው ያገለግላሉ። እኔ ተከልሁ፤ አጵሎስም አጠጣ፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ያሳድግ ነበር። . . ከእርሱ ጋር አብረን የምንሠራ ነንና» በማለት ጳውሎስን እንዲጽፍ ያደረገው ይኸው ነበር፤ (1ኛ ቆሮ. 3:4-6፣9)።

በቤተ ክርስቲያን ባሉ መሪዎች መካከል ጉላ ብሎ የሚታይ ልዩነት ካለ መንፈሳዊ ጥሬነትና ሥጋዊነት ለመኖሩ ማስረጃ ነው። መሪውም እኔ የተለየሁ ነኝ ብሎ የሚያስብ ከሆነ እንደ ሌሎቹ ሁሉ እርሱም ደካማነቱን እያሳየ ነው ማለት ነው። እንዲህ ዓይነቱ ነገር ጳውሎስን አስደንግጦታል፤ በጥብቅም ተቃውሞታል። በመሠረቱ፤ በምናገለግላቸው ሰዎች መወደድ ክሩት የለበትም፤ ይሁን እንጂ ዓይኖቻቸውን ከጌታ ላይ አንሥተው አገልጋዩ ላይ እንዲያደርጉ ምክንያት ሊሆን ስለሚችል አደገኛ ነው። መንፈሳዊ መሪዎች

በሥራቸው ሊከበሩና ሊወደዱ ይገባል፤ ይህ ግን ወደ ማያስፈልግ ሙገሣና ውዳሴ እንዳያመራ መጠንቀቅ ያስፈልጋል።

አንድ መሪ የተሳካለት የሚሆነው የሰዎች ትኩረት ከእርሱ ይበልጥ ክርስቶስ ላይ እንዲሆን ማድረግ ሲችል ነው። እርግጥ ነው በሥራው መጠን ተገቢው ምስጋናና ማበረታቻ ቢሰጠው ነውር አይደለም፤ እንደ ጣዖት ሲያደርጉት ዝም ብሎ ከተመለከተና የሚሰነዘረውን ሙገሣ ሁሉ የሚቀበል ከሆነ ግን ችግር አለ ማለት ነው።

በሥራው ተወዳጅ መሆንን የማይፈልግ የትኛው መሪ ወይም ሰባኪ ነው? በመሠረቱ፣ ተወዳጅ አለመሆንን በራሱ ጽድቅ ወይም በጐ ምግባር አይደለም፤ ተወዳጅነትና ዝነኝነትን መፈለግ ግን ከባድ ዋጋ እንደሚያስከፍል መዘንጋት አይኖርብንም። «ሰዎች ሁሉ መልካም ሲናገሩላችሁ ወዮላችሁ» በማለቱ ኢየሱስ ይህን ግልጽ አድርጐታል። ከዚሁ ጋር አያይዞም፦ «ሲነቅፏችሁና ሲያሳድዷችሁ በእኔም ምክንያት ክፉውን ሁሉ በውሸት ሲናገሯችሁ ብፁዓን ናችሁ» በማለት የተናገረውን እውነት መዘንጋት የለበትም።

በአንድ ወቅት ስቲፈን ኔል የተባሉ ጳጳስ ለሥነ መለኮት ተማሪዎች ሲናገሩ «ሰዎችን በቀላሉ ወደ መንፈሳዊ ትዕቢትና በመጨረሻም ወደ ጥፋት የሚወስድ በመሆኑ ታዋቂና ዝነኛ መሆን አደገኛ ነው። ከዓለም ጋር ለመደራደርና ተስማምቶ ለመኖር ከፍተኛ ዋጋ የሚያስከፍል በመሆኑ እንዲህ ያለውን ዝንባሌ በንቃት መከታተል ይኖርብናል» ብለዋል።

ታላቁ ሰባኪ ስፐርጂንም ታዋቂነትና ስኬት ስለሚያስከትሉት አደጋ ሲናገር፦

> «አንድ ሰው የተሳካለት ሲሆን ለሰዎች ዓይንና ሙገሣ ይጋለጣል፤ ከዚህም የተነሣ በየትኛውም ሥጋዊ ዘዴ ተጠቅሞ ለራሱ ጥቅምን ለማጋበስ ይፈተናል፤ በመጨረሻም ጨቋኝና ሁሉን ለእኔ ባይነት ምኞትን ያዳብራል። ሥራዬን ያቃናልኝ እግዚአብሔር መሆኑን እስካልተረዳሁ ድረስ፣ ያለ እኔ አስተዋጽኦ የእርሱ ሥራ ሊቀጥል እንደሚችል እስካልተገነዘብኩ ድረስ ማንኛውም ዓይነት ስኬት ከእኔ ይራቅ» አለ።

ጆርጅ ዋይት ፊልድ የተባለ ሰባኪ በሄደበት ሁሉ ከፍተኛ ዝናና ታዋቂነት ነበረው። በኋላ ግን ታዋቂነቱ እያስጠላው ስለመጣ ያለምንም ጋጋታና አጀብ ብቻውን ሆቴል ገብቶ መመገብ በሚችል ሰው መቅናት ጀምሮ ነበር። ይሁን እንጂ ያንንም ማድረግ አልቻለም። አገልግሎቱን በጀመረ ጊዜ በሰዎች መናቅ ለእርሱ ሞት መሆኑን፣ ይናገር ነበር።

በኋላ ግን «ዝነኛ ወይም ታዋቂ መሆንን እስኪበቃኝ ድረስ አይቻለሁ፤ አሁን ግን እያስጠላኝ መጥቶአል» ነበር ያለው።

ዝነኝነትና ታዋቂነት ስለሚያስከትሉት አደጋ ምክር ለሰጠው ሰው ሊመልስ «ወዳጄ፣ በጣም አመሰግንሃለሁ። ነፍሴን ከሞት ለመታደግ ስለ ሰጠኸኝ ምክርም እግዚአብሔር ይባርክህ። ጠላቶቼ በእኔ ላይ ስለ ሚያስወሩት ክፉ ወሬን በተመለከተ ግን እነርሱ ከሚናገሩት ይልቅ ስለ ራሴ ብዙ መጥፎ ነገሮችን አውቃለሁ» አለ።

ምንም እንደማይሳሳት የማሰብ ፈተና ሊገጥመው ይችላል።

አንድ ሰው መንፈሳዊ ነው ማለት ጨርሶ አያጠፋም አይሳሳትም ማለት አይደለም። መንፈስ ቅዱስ በእርሱ ውስጥ በመኖሩ፣ በመንፈስም መመራት በመፈለጉ ከሌሎች ይልቅ እንደ እግዚአብሔር ዓላማና አሳብ ሊኖር እንደሚችል ግልጽ ነው። ይሁን እንጂ በዚህ ዓለም እስካለ ድረስ አላጠፋም፣ አልሳሳትም ማለት አይችልም። ሌላው ቀርቶ በመለኮት የተጠሩና በአስደናቂ መንገድ በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ ሐዋርያት እንኳ እርምት የሚያሻው ስሕተትን ፈጽመዋል።

እግዚአብሔርን የሚያውቅ፣ ምናልባትም አብረውት ካሉ ሁሉ ይልቅ ስለ እግዚአብሔር ነገሮች በሚገባ የተረዳ መንፈሳዊ መሪ ሳያውቀው በዚህ ችግር ሊጠቃ ይችላል። የሚያቀርበው አሳብና ያለው አመለካከት ብዙ ጊዜ ትክክል ሆኖ መገኘቱ፣ ከሌሎች ይልቅ ስለ እነርሱ መጸለዩ፣ ማሰቡና መንፈሳዊ ተጋድሎ ማድረጉ፣ እሳሳታለሁ፤ አጠፋለሁ ብሎ እንዳያስብ ሊያደርገው ይችላል፤ የሌሎችን ምክርና ተግሣጽ አልቀበልም ወደ ማለትም ሊመራው ይችላል። እርግጥ ነው አቋም ያለው ሰው ሊሆን ይገባል፤ ለሚያምንበትም ነገር ያለ ማወላወል መቆም ይኖርበታል፤ ይሁን እንጂ፣ ይህ ሁልጊዜ ትክክል ነኝ ወደሚል መደምደሚያ እንዳያደርሰው መጠንቀቅ አለበት። አንድ መሪ ሊሳሳት እንደሚችል ማመኑ፣ ሌሎች ወንድሞቹና እኅቶቹ የሚሰጡትን ምክርና አስተያየት መቀበሉ፣ ያለውን ተሰሚነት ይጨምርለታል እንጂ አይቀንስበትም። በሌሎች ዘንድ ተአማኒነትን የሚያሳጣው ሊሳሳት እንደሚችል አለመቀበሉ ነው። አንድ ሰው ሌሎች የሕይወት ገጽታዎቹን በተመለከተ ትሑት ቢሆንም፣ እንዲህ ያለ ዝንባሌ ሊኖረው መቻሉ በመጠኑም ቢሆን ግር የሚል እውነት ነው።

እኔን የመሰለ ሰው ማግኘት አይቻልም፤ ያለ እኔ አይሆንላቸውም በሚል አስተሳሰብ ሊፈተን ይችላል

ከፍተኛ ተሰሚነትና ከበሬታ ያላቸው ሰዎች ብዙውን ጊዜ እነርሱን የሚተካ የሚገኝ ስለማይመስላቸው በወቅቱ ስፍራቸውን ለሌሎች መልቀቅ አይፈልጉም። ለሌላ ተተኪ መስጠት ሲኖርባቸው ሥልጣናቸውን የሙጥኝ ብለው ይይዛሉ። ይህ ደግሞ ከየትኛውም ይልቅ በክርስቲያናዊ ሥራ መስክ እጅግ አደገኛ ነው። ሥልጣናቸውን መልቀቅ በማይፈልጉ ሽማግሌዎች ምክንያት የሥራው እድገት ይገታል። ዕድሜያቸው በዘጠናዎቹ ዓመታት ውስጥ ያሉ አንድ ሽማግሌ አገልጋይ አሁንም በአንድ ትልቅ ቤተክርስቲን የእሑድ ትምህርት ቤት ዳይሬክተር በመሆን እየሠሩ እንደሆነ የዚህ መጽሐፍ አዘጋጅ ያውቃል። ይህ ግን በእርግጥ እርሳቸውን ተክቶ መሥራት የሚችሉ ወጣቶች ስለሌሉ አይደለም። ምናልባትም የቤተ ክርስቲያኑ ባለ ሥልጣኖች ሐቁን በድፍረት ለመጋፈጥና እርሳቸውን በሌላ ልጅ እግር ሰው መተካት ባለመፈጋቸው ሊሆን ይችላል። በጣም የሚያሳዝነው ደግሞ አንዳንድ በቅንነት የተነሣሡ ወገኖች «እናንተን እኮ ሊተካችሁ የሚችል የለም» በማለት እንዲህ ያሉ ሰዎች በሥልጣናቸው እንዲቀጥሉ ማበረታታቸው ነው። እንደ እውነቱ ከሆነ ግን ዕድሜያችን እየገፋ በሄደ መጠን የራሳችንን ሥራ እንኳ በአግባቡ መገምገም ይሳነናል። የሚተካኝ የለም በሚል አስተሳሰብ አገልጋዩ ከሚገባ በላይ ለረጅም ጊዜ ቤተክርስቲያንን ቢመራ የዚያች ቤተ ክርስቲያንን ውድቀት ያፋጥናል። እንዲህ ያሉ ሰዎች ገና ሥራውን ከጀመሩበት ጊዜ አንሥቶ አባላቶቹ በጌታ መታመንን እንዲማሩና የወደፊት የሥራው ተረካቢ ሰዎችንም ማሠልጠን፣ መኰትኰትና ማሳደግ ይኖርባቸዋል።

አገልጋዩን የስሜት ላይና ታች ማለት ሊያጠቃው ይችላል

በየትኛውም የእግዚአብሔር ሥራ የተሰማሩ አገልጋዮች አንዳንድ ጊዜ ተስፋ መቁረጥና የሳላማ መጨናገፍ ይገጥማቸዋል፤ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በስሜታቸው ላይ ይወጣሉ፤ ሁሉም ነገር የተሳካላቸው ስለሚመስላቸው በጣም ደስ ይላቸዋል። እንዲህ ያለ የስሜት መዋዠቅ አገልጋዩን በጣም ስለሚጐዳው በስሜቱ ላይ መደገፍ የለበትም። ስሜቱ ከፍ ስላለ መፈንጠዝ፣ ስሜቱ ዝቅ ስላለ ደግሞ መተከዝ ተገቢ አይደለም። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ የትኛው ሊያስደስተን፣ የትኛው ሊያሳዝነን እንደሚገባ እርግጠኛ አንሆንም። ጌታ የላካቸው ሰባዎቹ አገልጋዮች ባገኙት ስኬት ከመጠን በላይ ደስ ብሎዋቸው ነበር

የተመለሱት። ኢየሱስ ግን «አጋንንት ስለ ተገዙላችሁ ደስ አይበላችሁ፤» በማለት ስሕተታቸውን ካስተካከለ በኋላ «ይልቁንም ስማችሁ በሰማይ ስለተጻፈ ደስ ይበላችሁ» ብሎአቸዋል (ሉቃ. 10፡20)። በነበረው ከፍተኛ ስፍራ ትምክህት ያደረበት ሰይጣን ዕጣ ፈንታ ምን እንደሆነ ሲያመለክትም፣ «ሰይጣን እንደ መብረቅ ከሰማይ ሲወድቅ አየሁ» አለ።

በቀርሜሎስ ተራራ ከፈጸመው አስደናቂ ሁኔታ በኋላ ኤልያስ በጣም አዝኖ ሞቱን ሲመኝ እንመለከታለን። ጌታ ደግሞ በአጉል ሁኔታ በዕድሉ መማረሩንና ለራሱ መቆርቆሩን ፍቅር ባልተለየው ሁኔታ አስተካከለ። በሥራ ብዛት የደከመውንና ሰውነቱ የዛለውን ነቢይ ወዲያውኑ መገሠጽና መንፈሳዊ ትምህርት መስጠት አልፈለገም። ይልቁንም ሁለት ጊዜ ለረጃጅም ሰዓቶች እንዲተኛ አደረገ፤ ሁለት ጊዜ የተሟላ ምግብን መገበው። ጥልቅ መንፈሳዊ ችግሩን የፈታለትና ዘላቂነት ያለው ትምህርትን የሰጠው ከዚያ በኋላ ነበር። ይህን ያህል የሚያዝንበትና ሞትን እስኪመኝ ድረስ የሚያማርርበት በቂ ምክንያት እንደሌለውም አሳየው። በጌዜው ያለሁ ነቢይ እኔ ብቻ ነኝ በማለት ቢያስብም ያኔም ቢሆን እግዚአብሔር ለበዓል ጕልበታቸውን ያላንበረከኩ ሰባት ሺህ የራሱ ሰዎች ነበሩት። ሕዝቡ ከምንጊዜም ይልቅ እውነተኛ መሪ ያስፈልጋቸው ነበር፤ ሁሉንም እርግፍ አድርጐ ከሸሸ እነዚያን ሰዎች ያለ መሪ ሊያስቀራቸው ነው።

የእግዚአብሔርን ሥራ በተመለከተ ያለን እቅድ ሁሉ በተግባር ይፈጸማል ማለት እንዳልሆነ መገንዘብ አለብን። የምንወዳቸውና የምንንከባከባቸው ጣዖታት የሆኑብን ነገሮች እንደ ሸክላ ዕቃ ፍርክስክሳቸው ይወጣል። የተደገፍንባቸው ሰዎችም የተቀጠቀጠ ሸንበቆ መሆናቸው ይገለጣል። የቱንም ያህል ከፍተኛ መሥዋዕትነት የተከፈለበት ቢሆን እንኳ አንዳንድ ጊዜ ሰዎች የመሪነት ኃላፊነታችንን ሊቃወሙ ይችላሉ። እውነተኛ መንፈሳዊ መሪ ግን እንዲህ ያለ ሁኔታ ሲገጥመው የትካዜውና ተስፋ መቁረጡ ምንጭ ምን እንደሆነ መርምሮ ስለሚደርስበት ሁሉንም እንደ አመጣጡ ይቀበላል።

> «ዶክተር ኤፍ. ቢ. ሜየርን በቅርቡ የሚያውቅ ማንኛውም ሰው ነገሮችን በብሩህ ገጽታቸው የሚመለከቱ፣ በተስፋ የተሞሉና በመጨረሻ መልካም ነገር በክፉ ነገር ላይ ድል እንደሚጐናጸፍ ጽኑ እምነት እንደነበራቸው ይረዳል። እርሳቸው የዚህ ዓይነት አመለካከት የነበራቸው ከመሆኑም በላይ ሌሎችም የዚህ ዓይነት አመለካከት እንዲኖራቸው የማድረግ ችሎታቸውንም ይገነዘባል። ይሁን እንጂ፣ እንደ ማንኛውም ሰው

መንፈሳዊውን መሪ ሊገጥሙት የሚችሉ አንዳንድ ፈተናዎች

ሁሉ የሚያሳዝንና ተስፋ የሚያስቆርጥ ነገርም ሥጦአቸዋል። ዓይኖቻቸው ግን ምን ጊዜም በነገሮች ብሩህ ገጽታ ላይ ስለነበሩ ሕይወትን አጨልሞ የመመልከት ዝንባሌ አይገዛቸውም ነበር። ስለሆነም አንዱ ከፍ ሌላ ጊዜ ደግሞ ዝቅ በማለት የሚዋዥቅ አመለካከት አልነበራቸውም።»

እኚህ ሰው የእኛ ዓይነት ስሜቶች ቢኖሩዋቸውም፣ አመለካከታቸውን ሽንፈትና ውድቀት ላይ ብቻ አላደረጉም።

ብዙ ጊዜ አገልጋዮችን የሚያጠቃ ሌላ ዓይነት የመጫጫን፣ የመደበትና ተስፋ የመቁረጥ ስሜትም አለ። ይህን በተመለከተ ሲ. ኤች ስፐርጂን «አገልጋዩን የሚገጥሙት ደስ የማይሉ ወቅቶች» በሚል ርዕስ ባደረገው ንግግር እንዲህ ብሏል፦

ማንኛውንም ትልቅ ቁም ነገር ከማከናወናችን በፊት አንዳንድ ደስ የማይሉ ስሜቶች ሊገጥሙን ይችላሉ። በለንደን ያለውን ቤተ ክርስቲያን በመጋቢነት መምራት በጀመርኩ ጊዜ የዚህ ዓይነት ስሜት ያጠቃኝ እንደነበር አስታውሳለሁ። ምንም እንኳ በሥራዬ የተሳካልኝ ቢሆንም፣ ያ ራሱ የኃላፊነቴን ክብደትና ጥልቀት ስለሚያሳስበኝ በደስታ ከመፈንጠዝ ይልቅ ይበልጥ ያስጨንቀኝ ነበር። ለመሆኑ ይህን የሚያህል ብዙ ሕዝብ ለመምራት እኔ ማን ነኝ? በማለት ራሴን እንድጠይቅ ያደርገኛል። ወደ ትውልድ መንደሬ ተመልሼ ማንም ሳያውቀኝ መኖርን ተመኘሁ፤ ከመታወቅ ይልቅ አለመታወቅን ፈለግሁ። ይሁን እንጂ ብርሃን የበራልኝና የወደፊት አገልግሎቴ ብሩህ ገጽታ የታየኝም ያኔ ነበር። ጌታ ለትልቅ አገልግሎት ሲያዘጋጀኝ፣ በፊቴም ሰፊ በር ከመክፈቱ በፊት የዚህ ዓይነት ደካማነትና ለሥራው ብቁ አለመሆን ስሜት ሲያጠቃኝ እግዚአብሔር ለትልቅ በረከት እያዘጋጀኝ መሆኑን ተረድቼአለሁ።

አንዳንድ ጊዜ ነገሮች ሁሉ ይሳኩልናል፤ እኛ ከጠበቅነውም በላይ ይከናወኑልናል። በአገልግሎታችን የእግዚአብሔር መንፈስ ይንቀሳቀሳል፤ ነፍሳት ይድናሉ፤ ክርስቲያኖችም ይባረካሉ። በሳልና አስተዋይ መሪ ነገሮች ሲሳኩለትና ሲከናወኑለት ክብሩን መውሰድ የሚገባው ማን መሆኑን ይገነዘባል። ሮበርት ሙሬ ምክቼኒ የተባለ በውጭ አገር ያገለግል የነበረ ሚስዮናዊ እንዲህ ያለ የአገልግሎት መሳካትና መከናወንን ከተለማመደ በኋላ ወደ አገሩ ሲመለስ ይንበረከክና ክብሩን ሁሉ ለጌታ የመስጠት ልማድ ነበረው፤ መሆን ያለበትም ይኸው ነው። ሳሙኤል ቻድዊክ ደግሞ «ስኬትህ ከመጠን

በላይ አያስፈንጥዝህ፤ ውድቀትህም ተስፋ አያስቆርጥህ» የሚል አነጋገር ነበረው።

ነቢይ ወይስ መሪ?

አንዳንድ ጊዜ አገልጋዩ ለሁለት የተለያዩ የአገልግሎት ዘርፎች ብቁ ሆኖ ሊገኝ ይችላል። የትኛውን እንደሚመርጥም ይቸገራል። ለምሳሌ ያህል በቤተ ክርስቲያኑ ወይም በሚያገለግልበት ድርጅት የመሪነት ችሎታውን ያስመሰከረ ሰባኪ «ጥሪዬ የትኛው ነው? ሰዎች የሚያደንቁት መሪ ወይስ ደግሞ ሰዎች የማይወዱት ነቢይ?» በማለት ከሁለቱ የቱን መምረጥ እንዳለበት ሊቸገር ይችላል።

አንድ ታላቅ አገልጋይ የዚህ ዓይነቱን ሁኔታ በሚከተለው መንገድ ገልጦታል፦

> «ውጤቱም ምንም ይሁን ምን አንድ ሰባኪ እግዚአብሔር የሚሰጠውን መልእክት ብቻ እንደሚሰብክ ነቢይ መሆን አለበት። በሚያገለግልበት ቤተ ክርስቲያን ወይም የሃይማኖት ተቋም ያለውን የመሪነት ብቃት ሰዎች ሲገነዘቡለት በአገልግሎቱ ግጭት ይፈጠራል። ከሁለት አንዱን፤ ማለት የሰዎች መሪ መሆንን ወይም ደግሞ የእግዚአብሔር ነቢይ መሆንን፡ መምረጥ ይኖርበታል። በአንድ ጊዜ ነቢይም መሪም ለመሆን ከፈለገ ግን በሁለቱም ሳይሳካለት ይቀራል። መሪነቱን ሳይተው በዚያ ላይ የነቢይነቱን ሥራ ደርቦ መሥራት የሚፈልግ ከሆነ ደግሞ ከሰዎች ጋር ተመሳስሎ የሚኖር እንጂ ነቢይ መሆኑ ይቀራል። የአስተዳደሩን ሥራ ብቻ የሙጥኝ ብሎ ከያዘ ደግሞ እንደ ፖለቲከኛ ሁሉ ለሥልጣንና ለደረጃው የሚቆረቆር ይሆናል።»

እርግጥ ነው፤ በሁለቱ መካከል ያለውን ልዩነት ጥርት ባለ ሁኔታ ማየቱ የሚባለውን ያህል ቀላል ላይሆን ይችላል። አንደኛው ሌላኛውን የግድ ማስወገድ አለበት ማለትም አይደለም። ይሁን እንጂ፤ አንድ ወቅት ላይ ከመንፈሳዊ አገልግሎቱና ከአስተዳደር ሥራው የግድ አንዱን መምረጥ ሊኖርበት ይችላል፤ ሁለቱንም በአንድነት ማከናወን የማይችልበት ደረጃ ላይ ሊደርስ ይችላል፤ ትልቁ ችግር የሚነሳውም እዚህ ላይ ነው።

ባለፈው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ ላይ ግማሹን የዓለማችንን ክፍል በዳሰሰ ታላቅ መንፈሳዊ መነቃቃት እግዚአብሔር የተጠቀመባቸው ዶክተር አር. ኤ. ቶሪ እንዲህ ያለ ሁኔታ ገጥሞአቸው እንደነበር አንድ ጸሐፊ እንዲህ በማለት ተናግሮአል፦

እኚህን አገልጋይ ያደመጡ ሁሉ ሰውየውንና መልእክቶቻቸውን መለየት ችለዋል። መጽሐፍ ቅዱስን ይወድዳሉ፤ እውነተኛ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑንንም በሙሉ ልባቸው ያምናሉ፤ በታላቅ ቅንዓትና ተነሳሽነትም ሲሰብኩት ኖረዋል። ከእምነትና ከአቋማቸውም የሚያወላውሉ አልነበሩም። በአንድ ወቅት ከእግዚአብሔር ነቢይነትና የሰዎች መሪ ብቻ ከመሆን አንዱን መምረጥ ነበረባቸው፤ እርሳቸውም የሰዎች መሪ ከመሆን ይልቅ የእግዚአብሔር ነቢይ መሆንን መርጠዋል፤ የአገልግሎታቸው ስኬት መሠረትም ይኸው ነበር።

መንፈሳዊው መሪ ውድቅ ወይም ብቁ ሆኖ ያለመገኘት ስሜት ሊያድርበት ይችላል

ምንም እንኳ ከፍተኛ መሥዋዕትነት የከፈለ ቢሆንም፤ ክርስቶስን በማገልገል ገደብ የለሽ ስኬት ቢያስመዘግብም፤ ወንጌልን ለሌሎች ከሰበከ በኋላ እርሱ ራሱ እንዳይጣል በጳውሎስ ልብ ውስጥ ስጋት ነበር (1ኛ ቆሮ. 9:27)። ይህ ጳውሎስን ያሳስበው እንደነበር ሁለ እንዲህ ያለ መንፈሳዊ ኃላፊነት የተጣለባቸውንም ሁሉ ሊያሳስባቸው ይገባል። ከፍተኛ ተግባርን ያከናወነ ብዙ ልምምዶች ያሉት ሰው ቢሆንም፤ ይህ ጳውሎስን በዚሁ ረክቶና ተደላድሎ እንዲቀመጥ አላደረገውም፤ ውድቅ ሆኖ ከመገኘት ነጻ እንደሚያደርገውም ጨርሶ አላሰበም።

«የተጣልሁ» የሚለው ቃል አንድ የብረት ዓይነት ለአንድ ሥራ ብቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ከተፈተነ በኋላ ብቁ ሆኖ ሳይገኝ ሲቀር የታሰበለትን ወይም የታቀደለትን ዓላማ ባለማሟላት መጣልን ወይም ከጥቅም ውጪ መሆንን ያመለክታል። እዚህ ላይ ጳውሎስ ማሳየት የፈለገው ዋናው አሳብ ከውድድሩ በኋላ ሽልማት ወይም ዋጋን ስለማግኘት እንጂ ጨርሶ ከውድድሩ መስክ ስለ መገለል አለመሆኑን ከዐውደ ምንባቡ መረዳት ይቻላል። ውድድሩ የሚጠይቀውን መስፈርት አሟልቶ ካልተገኘ አሸናፊ ሊሆን ብሎም ሽልማትን መቀበል አይችልም።

ጳውሎስ ሁለት ድርሻ እንዳለው አድርጉ ነበር ራሱን የሚመለከተው። በአንድ በኩል ራሱ ተወዳዳሪ ነው፤ በሌላ በኩል ደግሞ የውድድሩን ሕግና ደንብ ለሌሎች ያስተዋውቃል፤ ሌሎችን ወደ ውድድሩ ይጋብዛል። ወንጌልን ለሌሎች ከሰበክሁ በኋላ ሲል ይህንኑ ማለቱ ነው። እንግዲህ የጳውሎስ ትልቁ ስጋት ወደ ውድድሩ ሌሎችን ከጋበዘ በኋላ በዚያው መስፈርት ሲመዘን እርሱ ራሱ የተጣለ ወይም ውድቅ ሆኖ እንዳይገኝ ነበር። እንዲህ ከሆነ ደግሞ ወንጌልን ለሌሎች

ለመስበክ የነበረው ጥሪ በከፍተኛ ደረጃ ውርደቱን አጉልቶ ከማሳየት ውጪ ምንም አይጠቅመውም ማለት ነው።

እዚህ ላይ የሚያነሳው ውድቀት ከሥጋ ጋር ተያያዥነት ባለው ሁኔታ ነው፤ ስለሆነም ሥጋውን በሥርዓት መግራት ወይም ለሥርዓት ማስገዛትን በጣም አስፈላጊ ሆኖ አግኝቶታል። ቻርለስ ሆጅ የተባሉ የሥነ መለኮት ምሑር እንደሚሉት በቅዱሳት መጻሕፍት መሠረት ሥጋ፦ «የኃጢአትና የኃጢአተኛ ባሕርይ ማደሪያ ነው። እዚህ ላይ ጳውሎስ አስገዘዋለሁ የሚለው ስሜታዊ ተፈጥሮውን ብቻ ሳይሆን በልቡ ውስጥ ያለውን ኃጢአት ጭምር ነው» ብለዋል።

ስለዚህ ከእንዲህ ዓይነቱ ጥፋት ለመዳን ጳውሎስ አካላዊ ባሕርያቱንም መግዛትና መቆጣጠር እንዳለበት ጭምር እንጂ የክርስቲያናዊ አስተምህሮው ትክክለኛነት ወይም የሥነ ምግባሩ ጥራት የትም ሊያደርሰው እንደማይችል በሚገባ ተረድቶአል ማለት ነው። «ልከኛ» የሚለው ቃል የሚያመለክተው ራስን መግዛትን፣ መግራትንና መቆጣጠርን እንጂ ሥጋን ያለ መጠን በመጨቆንና በሌላ በኩል ደግሞ ሥጋን ልቅ መተውን በተመለከተ ሚዛናዊነትን ስለ መጠበቅ ነው። የተለያዩ ምድራዊ ፍላጐቶቹን በማሟላት ሥጋው እንዲሰለጥንበት አልፈቀደም። «አስገዘዋለሁ» የሚለውም ቃል አንድ በጦር ሜዳ ድል ያደረገ መሪ ምርኮን እየነዳ ወደ አገሩ ሲገባ ያለውን ሁኔታ ያመለክታል። አንድ ሰው ይህን የጳውሎስን አባባል እንዲህ በማለት ተርጉመውታል «በውስጤ ያለውን እንስሳዊ ባሕርይ በመግራት ለሥርዓት አስገዘዋለሁ፤ እንደ ባሪያ አገዘዋለሁ እንጂ፣ እንደ ጌታ እንዲሰለጥንብኝ አልፈቅድለትም።»

22

ነህምያ፡- በምሳሌነት የሚጠቀስ መሪ

«አቤቱ አምላኬ በመልካም አስበኝ»
ነህምያ 13:31

መጽሐፍ ቅዱስ ከሚያነሳቸው መሪዎች መካከል ነህምያ በምሳሌነቱ ግንባር ቀደሙን ስፍራ ይይዛል። ምንም እንኳ አንዳንዱ የሚጠቀምባቸው ዘዴዎች ጠንከር ያሉ ቢመስሉም፣ በአጭር ጊዜ አስደናቂ ለውጥና ተሐድሶ በአገሩ ለማምጣት እግዚአብሔር ተጠቅሞበታል። ሰብዕናውንና የተጠቀመበት አሠራር ዘዴን ረጋ ብለን ስንመረምር ዘዴዎቹ ውጤታማ ሊሆኑ የቻሉት ጥራት ካለው ባሕርዩ ወይም ማንነቱ የተነሣ እንደነበር እንረዳለን።

ባሕርዩ ወይም ማንነቱ

ከነህምያ ሕይወት በመጀመሪያ የምንመለከተው የጸሎት ሰው መሆኑን ነው። ኢየሩሳሌም ስለ ነበረችበት ውድቀት ሲነገረው በመጀመሪያ ያደረገው በጸሎት ፊቱን ወደ እግዚአብሔር መመለስን ነበር፤ ይህም ወደ ጸጋ ዙፋን ለመቅረብ የነበረውን የዘወትር ልምድ ያመለክታል። መጽሐፉን ስናነብም እዚህና እዚያ ያቀረባቸውን አጫጭር ጸሎቶችን እንመለከታለን። ለእርሱ ጸሎት ማለት ወቅትን ወይም ጊዜን ጠብቆ የሚደረግ ሳይሆን ከዕለት ተዕለት ሕይወትና ሥራው ጋር በጣም የተያያዘ ጉዳይ ነበር (1:4፣ 6፣ 2:4፣ 4፣ 9፣ 5:19፣ 6:14፣ 13:14፣ 22፣ 29)።

በከፍተኛ ችግርና አደጋ ፊት ደፋር ሆኖ ተገኝቶአል። ሸሽቶ ነፍሱን እንዲያድን በአንድ ወቅት ለቀረበለት ምክር ሲመልስ «እንዲህ ያለ ሰው የሸሸና ነፍሱንስ ያድን ዘንድ መቅደስ የገባ ማን ነው? እኔስ አልገባም» ነበር ያለው (6:11)። እንዲህ ያለው ድፍረቱና ቆራጥነቱ የላሸቀውን የተሕዝቡን ወኔ ለማነሣሣት ከፍተኛ ድርሻ ነበረው።

ለሕዝቡ ደኅንነት ያለውን አሳቢነትና ተቆርቋሪነት አሳይቶአል፤ ይህም ወዳጆቹ ብቻ ሳይሆኑ ተቃዋሚዎቹም የመሰከሩለት ሐቅ ነበር። «ለእስራኤል ልጆች መልካሙን ነገር የሚሻ ሰው እንደመጣ በሰሙ ጊዜ እጅግ ተበሳጩ» (2:10)። ምን ያህል የሕዝቡ ጥፋት የተሰማው መሆኑንም ከጸሎቱ፣ ከጾሙና በእግዚአብሔር ፊት ካፈሰሰው እንባ መመልከት ይቻላል (1:4-6)። የሕዝቡን ሀዘንና ብሶት ከመጋራቱም

በላይ የኃጢአታቸውም ተካፋይ አድርጉ ነበር ራሱን ያቀረበው፤ ስለዚህም ሲጸልይ «በአንተ ላይም ያደረግነውን የእስራኤልን ልጆች ኃጢአት እናዘዝልሃለሁ፤ እኔና የአባቴም ቤት በድለናል» አለ (1፡6)።

ባለ *ራእይና ለነገሮች ጥርት ያለ እይታ* የነበረው መሆኑን አሳይቶአል። በንጉሡ ፊት ሞገስ ማግኘቱንና ትኩረቱን እንደሳበ ካረጋገጠ በኋላ ለሚሄድባቸው አካባቢዎች የትብብር ደብዳቤ እንዲጻፍለት ጠየቀ። በዚህም ብቻ ሳይወሰን በኢየሩሳሌም የሚጠብቀውን ከባድ *ሥራ* ግምት ውስጥ በማስገባት ለንጉሡ ደን ጠባቂ ደብዳቤ እንዲጻፍለትም ጭምር ጠይቆአል። «ለከተማውም ቅጥር. . . እንጨት እንዲሰጠኝ ለንጉሡ ዱር ጠባቂ ለአሳፍ ደብዳቤ ይሰጠኝ አልሁት» (2፡8)። ይህም የሚያሳየው ምን ያህል በጥንቃቄና ራቅ አድርጉ የሚያስብ መሆኑን ነው።

ለሚሠራው ሁሉ ተገቢውን ጥንቃቄና ቅድመ ዝግጅት የሚያደርግ ሰው ለመሆኑ ካደረጋቸው እንቅስቃሴዎች *መመልከት* ይቻላል። ኢየሩሳሌም እንደደረሰ ወዲያውኑ *ሥራውን* አልጀመረም። ይህንንም «ወደ ኢየሩሳሌምም ደረስሁ፤ በዚያም ሦስት ቀን ያህል ተቀመጥሁ» በማለት ከተናገረው *መረዳት* ይቻላል (2፡11)። በዚህ የጊዜ ክፍተት መካከል ሁኔታውን በሚገባ ካጠና፣ ነገሮችን በጥልቀት ካገናዘበ በኋላ ነበር *ሥራ* የጀመረው። ይህም ሆኖ እንኳ በጣም ጠንቃቃ ከመሆኑ የተነሣ *የመጣበትን* ጉዳይ ለማንም አልተናገረም፤ ያም ሆኖ፣ ጥናቱን የሚያካሂደው ጨለማን ተገን በማድረግ ነበር።

ነህምያ የማያወላውልና ግልጽ ውሳኔ በማድረግ ይታወቃል። ውሳኔ ማድረግ ሲገባው ከዛሬ ነገ በማለት አላመነታም። ቆራጥና ብርቱ ባሕርዩ ለወሳዋይነት ወይም *መደረግ* ያለበትን ነገር ለማዋል ለማሳደር አይፈቅድለትም።

ነህምያ የሌሎች ችግር የሚገባውና የሚያሳስበው ሰው ነበር። የሕዝቡን ብሶትና ችግር ለመረዳት ርኅራኄ ባልጐደለው ሁኔታ ረጋ ብሎ ያዳምጣል፤ የመፍትሔም እርምጃ ይወስዳል (4፡10-12፣ 5፡1-5)።

ነህምያ የሚያደርጋቸው ውሳኔዎችና የሚወስዳቸው እርምጃዎች ለአድልዎ ወይም *ለወገንተኛነት መንፈስ* የጠሩ ነበሩ። በፍጹም ሰዎችን ከሰዎች አያበላልጥም። ሹማምንትም ሆኑ ተራ ሰዎች በእርሱ ፊት እኩል ነበሩ። «ታላላቆቹንና ሹማምንቱንም ተጣላኋቸው፤ ትልቅም ጉባዔ ሰበሰብሁባቸው» ሲል ይህንኑ ነው የሚያመለክተው (5፡7) ነገሮችን ከመንፈሳዊ እይታ አንጻር መመልከቱ በገሃድ ከሚታየው ሐቅ እንዲሸሽ አላደረገውም። «ወደ አምላካችን ጸለይን. . . ጠባቂዎችንም

በሌሊትና በቀን አደረግን» (4:9)። የተቀበለው ኃላፊነት ከሚያስከትለው ውጣ ውረድና ጥረት እንዲሸሽ አላደረገውም፤ ይልቁንም ችግሩን በመጋፈጥ ያስበውን ለማሳካት በትጋት ሲሠራ ነበር።

ነህምያ ተፈትኖ የወጣ ጠንካራ የአስተዳደር ሰው ነበር። በውጣ ውረዱ ላይናወጥ፣ አደጋን ያለፍርሃት ተጋፍጦአል፤ በውሳኔው ቆራጥ ነበር፤ በአመራር ብቃቱ የተዋጣለት ነበር፤ በተቃዋሚዎች ፊት አልተሸበረም፤ ዛቻ አላስበረገገውም፤ ተንኰለኞችን በንቃት ተከታትሎአል፤ ከሁሉም ይልቅ ደግሞ የተከታዮቹን አመኔታና ከበሬታ ያገኘ መሪ ነበር።

የአሠራር ዘዴዎቹ

አብረውት የነበሩትን ሰዎች ወኔ *የሚቀሰቅስና የሚያነሣሣ* ነበር። ይህ የአንድ ኃላፊነት የሚሰማው ሰው ዋነኛ ተግባር ነው። ይህንንም ማድረግ የቻለው እምነታቸውን በማነሣሣትና የትኩረት አቅጣጫዎቻቸውንም ከችግሮቻቸው ላይ አንሥተው በእግዚአብሔር ትልቅነትና ታማኝነት ላይ እንዲያደርጉ በማስቻል ነበር። መጽሐፉ ውስጥ በተደጋጋሚ የምናገኛቸው አሳቦችም ይህንኑ የሚያጸኑ ናቸው።

«የሰማይ አምላክ ያከናውንልናል» (2:20)

«አትፍሯቸው ታላቁንና የተፈራውን ጌታ አስቡ» (4:14)።

«አምላካችን ስለ እኛ ይዋጋል» (4:20)።

«የእግዚአብሔር ደስታ ኃይላችሁ ነውና» (8:10)።

እምነት እምነትን ይወልዳል። ጨለምተኝነት እምነትን ያደክማል፤ አብረውት ላሉ ወይም ለሥራ ባልደረቦቹ እምነትን *መመገብ* የአንድ *መንፈሳዊ መሪ* ዋነኛ ኃላፊነት ነው።

ነህምያ የሚያበረታታና የሚያደፋፍር ሰው ነበር። *መጀመሪያውኑ* የመጣው ተስፋ ቆርጠውና ወኔያቸው ወደ ላሽቀ ሕዝብ እንደመሆኑ መጠን፤ ተቀዳሚ እርምጃውም የሕዝቡን ተስፋ ማጫርና ተባባሪነታቸውን ማግኘት መሆን ነበረበት። በከፊልም ቢሆን ይህን ያደረገው በእርሱ ላይ ስላለች የእግዚአብሔር እጅ መልካምነትና በጐነት ለሕዝቡ በመናገሩ ነበር፤ ያለውን ራእይና በእግዚአብሔር ያለውን እምነት በማካፈል ነበር። «የአምላኩም እጅ በእኔ ላይ እንደሆነች ንጉሡም የነገረኝን ቃል ነገርኋቸው፤ እነርሱም እንነሣና እንሥራ አሉ» (2:18)።

ስሕተትና ውድቀት በጊዜው *መታረም* ይኖርበታል፤ ይሁን እንጂ ያንን የምናደርግበት መንገድም በጣም ወሳኝ ነው። ነህምያ የሰዎችን

ስሕተት ያሳየው ማረም በሚችሉበትና ለተሻለ ነገር በሚነሣሡበት ሁኔታ ነበር። ከዚህም በላይ ታማኝነቱና ራስን የመግዛት ችሎታው ሕዝቡ እምነት እንዲጥሉበት፣ ሥልጣኑንም እንዲቀበሉለት አድርጐአቸዋል።

ችግር ያስከትላሉ ብሎ የሚያስባቸውን ጉዳዮች በሚገባ ለማስተናገድ የራሱንና የሌሎችን ልብ አዘጋጅቶአል። ይህንን ከሚከተሉት ሁለት ምሳሌዎች መመልከት ይቻላል።

በሥራው ብዛትና በሚገጥማቸው ተቃውሞ የሕዝቡ ወኔ ዝሎ ነበር (4፡10-16)። በጣም ደክመዋል፣ በየቦታው የተከመረው ፍርስራሽ ወደፊት እንዳይገፉ አደናቅፎአቸዋል፤ በዚህ ላይ ጠላቶቻቸው ዛቻና ማስፈራሪያ ይሰነዝሩባቸዋል። ታዲያ፣ ይህን ሁሉ ለማስተካከል ነህምያ በምን ዓይነት ዘዴ መጠቀም ነበረበት? አሳባቸውን ሁሉ እግዚአብሔር ላይ እንዲያሳርፉ አደረገ። አስፈላጊውን መከላከያ መሣሪያ እንዲይዙ አደረገ። በምድብ በምድብ አድርጐ ቁልፍ ቁልፍ ቦታዎችን አስያዛቸው። ከፊሉን ወደ ሥራ አሠማራ፤ ከፊሉ ደግሞ የጥበቃ ሥራ እንዲያከናውኑ፣ ከፊሉን ደግሞ እንዲያርፉ አደረገ። ተገቢውን ግምት የሚሰጣቸውና ችግሮቻቸውንም የሚጋራቸው መሪ እንዳገኙ ሲረዱ የሕዝቡ ወኔና ድፍረት ተነቃቃ።

በሁለተኛ ደረጃ፣ ባለጸጋ ወንድሞቻቸው በስግብግብነትና በጭካኔ ሌሎችን እየጨቆኑ መሆናቸውን በማየታቸው የሕዝቡ ተስፋ ጨልሞ ነበር (5፡1-5)። ድሆች ርስታቸውን በገንዘብ አስይዘዋል፤ ልጆቻቸው የአበዳሪ ባሪያዎች ሆነዋል። «ታላላቆችም ወይናችንን ይዘዋልና ልናድናቸውም አንችልም» እስኪሉ ድረስ በሁኔታው ተማርረዋል። ልጆቻቸው በጠላት እጅ ውደቀው ከማየት፣ ሊያድኗቸውም አቅም እንደሌላቸው ከመረዳት የበለጠ ሰዎችን ተስፋ የሚያስቈርጥ ነገር ሊኖር አይችልም።

አሁንም ነህምያ የተከተለው አሠራር ዘዴ ምሳሌነት ያለው ነው። በመጀመሪያ ደረጃ እሮሮና ብሶታቸውን ከልቡ አደመጠ፤ በደረሰባቸውም ችግር አዘነ። ነህምያ በዚህ ብቻ አልተወሰነም። በደሉን የፈጸሙትን ገሠጸ፤ የሕዝቡን ችግር ምክንያት በማድረግም ከወገኖቻቸው ያለ አግባብ ጥቅም ያጋበሱ ባለ ገንዘቦችንም አዋረደ (5፡7)። ስግብግብነታቸውን ከራሱ መሥዋዕታዊ ሕይወት ጋር በማነጻጸር ዘለፋቸው (5፡14)። ያለ አግባብ የወሰዱትን በአስቸኳይ እንዲመልሱ አደረገ (5፡11)። መንፈሳዊ ሥልጣኑን በሙሉ ልባቸው በመቀበላቸው «እንመልስላቸዋለን ከእነርሱም ምንም አንሻም» በማለት ቃል ገቡ (5፡12)።

ነህምያ፣ የእግዚአብሔር ቃል ሥልጣን ወደ ቀድሞ ስፍራው እንዲመለስ አደረገ (8:1-8)። ያ ባይሆን ኖሮ ያመጣው ለውጥ ወይም ተሐድሶ ለአጭር ጊዜ ብቻ ይሆን ነበር፤ ምናልባትም እውነተኛ ተሐድሶ ማድረግ ጨርሶ አይቻልም ነበር። የእግዚአብሔር ቃል ለነገር ሁሉ መለኪያና መስፈርት መሆኑን አሳየ፤ ለወሰደው እርምጃ መንፈሳዊ ሥልጣን ሊኖረው የቻለውም ከእግዚአብሔር ቃል የተነሣ ነበር።

ከኢያሱ ዘመን ወዲህ ተቋርጦ የነበረው የዳስ በዓል እንደገና እንዲከበር አደረገ (8:14)። ሳምንቱን ሙሉ እረፍት ሲያደርጉ እነዚያ በሥራ የደከሙ ወገኖች ምንኛ እፎይ ብለው ይሆን! የቅዱሳት መጻሕፍት በአደባባይ መነበብ ሕዝቡም ሆኑ ካህናቱ ኃጢአታቸውን እንዲናዘዙ አደረገ (9:3-5)። የረከሱ የጦቢያ ዕቃዎችን አውጥተው በመጣል ቤተ መቅደሱን አጸዱ፤ ወይም አነጹ (13:4-9)። ንዋየ ቅዱሳቱን ወደ ተገቢ ቦታቸው መለሱ (13:9)። አሥራታቸውን በማውጣት ወደ ቤተ መቅደሱ ግምጃ ገቢ እንዲሆን አደረጉ (13:5)። የሰንበት ዕረፍት እንደገና ተደነገገ (13:15)። ከአካባቢው አረማውያን ጋር ያደርጉት የነበረ ድብልቅ ጋብቻ ታገደ (13:23-25)። ሙሉ በሙሉ ከእነርሱ መለየት እንዳለባቸውም ተነገረ (13:30)።

ነህምያ፣ ሕዝቡንና ሁኔታዎችን በማደራጀት ረገድ የተዋጣለት መሪ ነበር። ዝርዝር እቅዶችን ከማውጣቱ በፊት ሁኔታዎችን በጥንቃቄ ያጠናል (2:11-16)። ለሥራው ብቁ የሚሆኑ ሰዎችን መረጠ። ለእያንዳንዱ ምድብ የተወሰነ ኃላፊነትን ሰጠ። አብረውት የሚሠሩትን ስለ መልካም ሥራቸው ስማቸውንና የቦታውን ስም እየጠራ ያመሰግናቸው ነበር። ስለዚህም ሰብዓዊ ፍጡራን እንጂ ሰው ሠራሽ ማሽን አለመሆናቸው እንዲሰማቸው አደረገ። ተገቢውን ሰው በተገቢው ስፍራ የማስቀመጥ ልዩ ችሎታ ነበረው። «ወንድሜን አናኒንና የግንቡን አለቃ ሐናንያን በኢየሩሳሌም ላይ ሾምኋቸው» (7:2)። ለእያንዳንዱ ሰው ሥራ በመስጠት የመሪነት ችሎታቸውን የሚያዳብሩበት ዕድል ይሰጥ ነበር። አብረውት ለሚሠሩ ላቅ ያለውን የእግዚአብሔር ቃል መስፈርት ያስቀምጥ ነበር፤ ታማኝነትን በተመለከተ «ታማኝ ነበር»፤ መንፈሳዊነትን በተመለከተ «ከብዙዎቹ ይልቅ እግዚአብሔርን የሚፈራ» ነበር።

በተደራጀ ሁኔታ የተነሣበትን ተቃውሞ በማስተናገድ በኩል የተለየ የመሪነት ብቃት እንደነበረው አሳይቶአል። ለምሳሌ ያህል አፍ አውጥተው የሰደቡት ነበሩ፤ የሚዝቱበትና የሚያስፈራሩት ነበሩ፤ ሰርጐ ገብ ሰዎችን በመላክ ሥራውን ሊያደናቅፉበት የሚሞክሩም

ነበሩ፤ ተንኰልና ሤራ የሚሸርቡበት መሰሪ ሰዎችን አስነስተውበታል። እንግዲህ በዚህ ሁሉ ጋሬጣና ውጣ ውረድ አልፎ የጀመረውን ሥራ ከዳር ማድረስ ከፍተኛ ጥበብና ማስተዋል መጠየቁ ግልጽ ነው።

በዚህ ሁሉ መሐል ነህምያ የወሰደው የመጀመሪያ እርምጃ ጸሎት ነበር። «ወደ አምላካችን ጸለይን» የሚለውም ይህንኑ ነው የሚያመለክተው (4:9)። ሁኔታው ምቹ ሲሆን ተቃዋሚዎቹን ችላ በማለት በሙሉ ልቡ ሥራውን ያካሂዳል። የሚነሣው ተቃውሞና ዛቻ በምንም ዓይነት ከሥራው አላዘናጋውም፤ ያም ሆኖ ግን በሚቻለው መጠን ጥንቃቄ ያደርግ ነበር (4:16)። ከሁሉም በላይ ደግሞ በእግዚአብሔር የነበረው እምነት አንድም ጊዜ እንኳ አልዋዠቀም (4:20)።

መንፈሳዊ መሪነት የሚፈተነውና የሚረጋገጠው የተጀመረው ሥራ ከግብ ሲደርስ ነው። ከነህምያ ሕይወት የምንመለከተውም ይህን ሲሆን መጽሐፉም እንዲህ በማለት ይመሰክራል-

«ቅጥሩም ተጨረሰ»

በመንፈሳዊ መሪነት ዙሪያ ሌሎች ጠቃሚ መጻሕፍት

«መንፈሳዊ መሪ» የተሰኘውን ይህን መጽሐፍ በማንብብዎ ብዙ እንደ ተማሩ ፣ ብዙም እንደተጠቀሙ እናምናለን:: እንደዚያ ከሆነ ደግሞ የክርስቲያናዊ መሪነት ግንዛቤዎን በማስፋት ረገድ ከፍተኛ እገዛ የሚያደርጉልዎትን የሚከተሉትን አራት መጻሕፍት እንዲያነቡ አጥብቀን እንመክራለን:-

1. መንፈሳዊ እውነታን መራብና መጠማት፣
2. የመስቀሉ መንገድ፣
3. ወደ ኋላ አልመለስም፣
4. ከፍቅር የሚገኝ ለውጥ

❖በመጋቢዎች (ፓስተሮች)÷ በወንጌላውያን ÷ በቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች÷ የተለየዩ ክርስቲያናዊ ድርጅቶችንና ቤተሰብን በመምራት ላይ ባሉ ወገኖች እጅ ሊኖር የሚገባው ድንቅ መጽሐፍ ——

“ይህን መጽሐፍ በእንግሊዝኛ ከረጅም ዓመታት በፊት አንብቤአለሁ፤ በትምህርቱም ብዙ ተጠቅሜአለሁ:: አሁን ደግሞ ጥራቱን በጠበቀ ደረጃ ወደ አማርኛ ተተርጉሞ ስመለከት ምን ያህል የአገልጋዮችን ሕይወት እንደሚያበለጽግ አውቃለሁና በጣም ደስ አለኝ:: በታሪክ ውስጥ የነበሩ የብዙ ታላላቅ የእግዚአብሔር ሰዎችን ሕይወትና ገጠመኝ ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት ጋር በማገናዘብ በአገልግሎታችን ተግባራዊ የምናደርግበትን መንገድ ያመለክታል::
በየትኛውም ክርስቲያናዊ ሥራ የተሰማራን ወገኖች ከዚህ መጽሐፍ ብዙ እንደምንጠቀም ስናገር በልበ ሙሉነት ነው:: በተለይም ደግሞ መሪዎችን ለማሠልጠን በሚደረግ ሙከራ የዚህ መጽሐፍ አስተዋጽዎ በቀላሉ የሚታይ አይሆንም

ብርሃኑ ሞገስ
የብርሃን መገናኛ ብዙኀን ክርስቲያናዊ አገልግሎት ዳይሬክተር

“ከአገራችን ዋና ዋና ተግዳሮቶች መካከል የአመራር ችግር አንዱና ዋናው መሆኑን ብዙዎች ይስማማሉ:: በዚህ አንገብጋቢ ወቅት ይህ “መንፈሳዊ መሪ” የተሰኘው መጽሐፍ በአማርኛ ተተርጉሞ ለሕዝባችን መቅረቡ ይህን ችግር ለመፍታት አብያተ ክርስቲያናት የሚያደርጉትን ጥረት በከፍተኛ ደረጃ እንደሚያግዝ አምናለሁ:: መጽሐፉ የመሪነትን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት በሚገባ በመዳሰስ ከአንድ እውነተኛ መሪ የሚጠበቁትን ባሕርያት በስፋት ያስተምራል:: አቀራረቡ ግልጽ ነው ÷መጽሐፍ ቅዱሳዊና ሕይወትን ለዋጭም ነው:: በየትኛውም የአመራር መስክ ያሉና ለመሪነት ራሳቸውን እያዘጋጁ ያሉ ቢያነቡት በእጅጉ ይጠቀማሉ::

LEADER

ማሙሻ ፈንታ
የፔንቲኮስታል ቲዮሎጂካል ኮሌጅ
ፕሪንሲፓል

ዋጋ 10.00 ብር